ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ማክሰኞ 84ኛ ዓመት ቁጥር 133 ጥር 13 ቀን 2017 ዓ.ም ዋጋ 34.50 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!









# በኢትዮጵያ በትራክተር የማረስ ምጣኔ 25 በመቶ ደረሰ

**በኃይሉ አበራ**

አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ በትራክተር የማረስ ምጣኔ ከነበረበት 5 ነጥብ ሰባት በመቶ ከ2012 ዓ.ም ጀምሮ በተሠሩ ተከታታይ ሥራዎች በአሁኑ ጊዜ 25 በመቶ መድረሱን የግብርና ሚኒስቴር አስታወቀ።

በግብርና ሚኒስቴር የግብርና መካናይዜሽን መሪ ሥራ አስፈጻሚ ተወካይ አቶ እሸቱ ሁንዴ ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ እንደተናገሩት፤ በኢትዮጵያ በትራክተር የማረስ ምጣኔ ከአምስት ዓመት በፊት ከነበረበት አምስት ነጥብ ሰባት በመቶ በፍጥነት በማደግ በአሁኑ ጊዜ 25 በመቶ ላይ ደርሷል።

የግብርና መካናይዜሽንን በግለሰብ ደረጃ ማስፋፋት ከዋጋ አኳያ አንድ ኮምባይነር 40 ሚሊዮን ብር አካባቢ በመሆኑ በባለሀብቶች ወይም በተደራጁ ወጣቶች በኩል የማስፋፋት


በኢትዮጵያ በትራክተር... ወደ ገጽ 4 ዞሯል




ካሣሁን ጎፌ (ዶ/ር)

## በስድስት ወራት ከወጪ ንግድ ሦስት ነጥብ 28 ቢሊዮን ዶላር ገቢ ተገኘ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- ባለፉት ስድስት ወራት ከወጪ ንግድ ከሦስት ነጥብ 28 ቢሊዮን ዶላር በላይ መገኘቱን የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ገለጸ፡፡

የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስትር ካሣሁን ጎፌ (ዶ/ር) በማኅበራዊ ትስስር ገጻቸው ባስፈሩት መልዕክት፤ ባለፉት ስድስት ወራት በወጪ ንግድ ዘርፍ ሦስት ነጥብ 28 ቢሊዮን ዶላር ገቢ መገኘቱን አስታውቀዋል።

የንግድ ምዝገባና ፍቃድ አሰጣጥ በኦንላይን እንዲሆን ውጤታማ ሥራ መሠራቱን አንስተው፤ በዚህ ረገድ ብልሹ


በስድስት ወራት... ወደ ገጽ 4 ዞሯል




ከተማ መስቀላ (ዶ/ር)

## በሰሜኑ ጦርነት የተጎዱ የ46 አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መልሶ ግንባታ ተጠናቀቀ


ገጽ4


# “በዲጂታሉ ዓለም ለመጠቀም ዲጂታል ማንነት መሠረታዊ ጉዳይ ነው”

**አብዮት ባዩ (ዶ/ር)**
**በኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር የሚኒስትሩ አማካሪ**

**ፍሬሕይወት አወቀ**

አዲስ አበባ፡- በዲጂታሉ ዓለም ለመጠቀም ዲጂታል ማንነት መሠረታዊ ጉዳይ ነው፤ ዲጂታል መታወቂያ ዲጂታል አገልግሎቶችን ለመጠቀም የማይተካ ሚና ያለው ሲሉ በኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር የሚኒስትሩ አማካሪ አብዮት ባዩ (ዶ/ር) ገለጹ፡፡

አብዮት ባዩ (ዶ/ር) በተለይም ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የፋይዳ ወይም የዲጂታል መታወቂያ ዋና ዓላማ አንድ ሰው ማንነቱ በትክክል ታውቆና ተለይቶ በተለይም በዲጂታል ዓለም ውስጥ መሥራትና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ እንዲኖረው ማድረግ የሚያስችል ነው፡፡

እሳቸው እንዳሉት፤ የፋይዳ ወይም የዲጂታል መታወቂያ ሂደት ከአጠቃላይ የሀገሪቱ የዲጂታል




ትራንስፎርሜሽን ዕድገት ጋር ጎን ለጎን መሄድ ያለበት ጉዳይ ነው፡፡ ምክንያቱም ዲጂታል መታወቂያውን ብቻ መጠቀም በራሱ የመጨረሻው ግብ አይደለም፡፡

ከዲጂታል መታወቂያ የሚገኙ ኢኮኖሚያዊ በረከቶችን ለመጠቀም ዋናው ነገር ዲጂታል መታወቂያውን ከማግኘት ባለፈ ሌሎች ዲጂታል የሆኑ አገልግሎቶችን መጠቀምና ዲጂታል መታወቂያን ዲጂታላይዝ ማድረግ የግድ እንደሆነ አብራርተዋል፡፡


በቀጣይ የዲጂታል ትራንስፎርሜሽን ሥራዎች ሁሉ ከዲጂታል መታወቂያ ጋር የሚተሳሰሩ እንደሆነ የጠቀሱት አብዮት ባዩ (ዶ/ር)፤ በተለይም የመንግሥት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ማንኛውንም አገልግሎት በሚያስቡበት ጊዜ ከዲጂታል መታወቂያ ጋር ማስተሳሰር እንዳለባቸው ተናግረዋል፡፡ ይህን ማስተሳሰር ሲቻል ሀገሪቷ ከዲጂታል መታወቂያ የበለጠ ተጠቃሚ ትሆናለች፡፡ ከዲጂታል መታወቂያ የሚገኘው ጠቀሜታም መሠረታዊና ዜጎችን ፍትሐዊ በሆነ መንገድ ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚ ማድረግ


“በዲጂታሉ ዓለም... ወደ ገጽ 4 ዞሯል






አቶ በልስቲ ፈጠነ


አቶ ስንታየሁ በፍቃዱ


ወ/ሮ ራሔል ለማ

# የሥርዓተ-ምሕዳር ግልጋሎት ክፍያ ሥርዓት ተግባራዊ እንዲደረግ ተጠየቀ

**ታምራት ተስፋዬ**

አዲስ አበባ፡- የአካባቢ የሥርዓተ-ምሕዳር ግልጋሎት ክፍያ ሥርዓት ተግባራዊ እንዲደረግ የአማራ እና የኦሮሚያ ክልሎች ጠየቁ፡፡ የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን በበኩሉ፣ የግልጋሎት ክፍያ ሥርዓት ተግባራዊ ለማድረግ የሕግ ማሕቀፍ ለማዘጋጀት እንቅስቃሴ ጀምሬአለሁ» ብሏል፡፡

የአማራ ክልል የአካባቢና ደን ጥበቃ ባለሥልጣን ምክትል ኃላፊ አቶ በልስቲ ፈጠነ እንደገለፁት፣ ኢትዮጵያ በብዝኃ ሕይወት ሀብት የታደለች ናት፡፡ ይሁንን የተፈጥሮ በረከት ጠብቆ ለማቆየትና ዘለቄታዊ ጥቅምን ለማረጋገጥ የሥርዓተ ምሕዳርን ዋጋ አጥንቶና ተመን አውጥቶ የክፍያ ሥርዓት በመዘርጋት በሚሰበሰበው ፈንድ ሀብቱ በዘላቂነት እንዲጠበቅ፣ እንዲለማና ጥቅም ላይ እንዲውል ማድረግ ላይ ድክመት ይስተዋላል፡፡

‹‹የሀብት ዋጋ ትመና ለምሳሌ የሃዋሳንና ጣናን ሐይቅ ብንወስድ በሁለቱ ሐይቆች ላይ ከቱሪዝም ጋር በተገናኘ ሆቴሎች አሉ፡፡ እነዚህ ሆቴሎች ከሀብቱ ይጠቀማሉ›› ያሉት አቶ በልስቲ፣ ይሁንና መልሰው ለአካባቢ ጥበቃና ዘላቂነት የሚያደርጉት አስተዋፅዖ እንደሌለ ጠቁመዋል።

ይህ ውስንነት መስተካከል እንዳለበትና ግልጋሎቱን የሚጠቀሙ ኢንቨስትመንቶች ለአካባቢ ጥበቃ አስተዋፅዖ ማድረግ እንዳለባቸው የገለጹት አቶ በልስቲ፣ ለዚህም የሥርዓተ-ምሕዳር ግልጋሎት ክፍያ ሥርዓት ተግባራዊ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን አስገንዝበዋል፡፡

የኦሮሚያ አካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን የአካባቢ ዘርፍ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ዳይሬክተር አቶ ስንታየሁ በፍቃዱ በበኩላቸው፣ ‹‹እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ሀገራት በነፃ ለሚገኙ ነገሮች ክብር፣ ዋጋና እንክብካቤ የመስጠት ድክመት ይስተዋላል፡፡ የሥርዓተ ምሕዳር ግልጋሎት ክፍያ በፍጥነት ተግባራዊ ከተደረገ መሰል ችግሮችን ማስቀረት ይችላል›› ብለዋል፡፡

መንግሥትም ሆነ ተቆጣጣሪ አካላት ከፍተኛ መዋዕለ ንዋይ እየመደቡ የጥበቃና እንክብካቤ ሥራቸውን ይቀጥሉ ማለት አግባብ እንዳልሆነ የጠቆሙት አቶ ስንታየሁ፣ ተቆጣጣሪ አካል ከመንግሥት በጀት ጥገኝነት መውጣትና ራሱን መቻል እንዳለበት አመላክተዋል፡፡ ለዚህ ደግሞ አገልግሎቱን የሚያገኙ አካላት ክፍያ እንዲፈፅሙ ማድረግ ወሳኝ መፍትሔ ስለ መሆኑ አስገንዝበዋል፡፡

በፌዴራል አካባቢ ጥበቃ የአካባቢ ሥነ-ምሕዳር ግልጋሎት ዋጋ ትመና፣ ጥናት እና የካርበን ክፍያ ቁጥጥር ዴስክ ኃላፊ ራሔል ለማ በበኩላቸው፣ ‹‹እንደ ሀገር የሥርዓተ ምሕዳር ዋጋ ትመናና ክፍያ ሥርዓት በመዘርጋትና ወደ ሥራ በመግባት ረገድ ዘግይተናል›› ብለዋል፡፡

በአሁን ወቅት ብሔራዊ የሥርዓተ ምሕዳር ግልጋሎቶች ትመናና ዋጋ ክፍያ ስትራቴጂ መቀረፁንና የሕግ ማሕቀፍ መዘጋጀቱን የጠቆሙት ኃላፊዋ፣ ይህ ረቂቅ አዋጅ የተሟላ ይዘት እንዲኖረው ምሑራንን ጨምሮ ከባለድርሻ አካላት ጋር ምክክር እየተደረገ ስለመሆኑም አስታውቀዋል፡፡ የሕግ ማሕቀፉ በዚህ ዓመት ተጠናቆ ተግባራዊ እንዲሆን በልዩ ትኩረት እንደሚሠራም አስረድተዋል፡፡

‹‹ብሔራዊ የሥርዓተ ምሕዳር ግልጋሎቶች ትመና እና ዋጋ ክፍያ ዓላማው ገንዘብ መሰብሰብ እንዳልሆነ አፅንዖት ሰጥተው ያስገነዘቡት ወይዘሮ ራሔል፣ የክፍያው ዓላማም ሥርዓተ ምሕዳሩን ለመጠበቅና ለመንከባከብ እንዲሁም በዚህ ተሳታፊ የሆኑና ጊዜና ጉልበታቸውን የሚሰጡ ማኅበረሰብ አባላት ከሀብቱ እንዲጠቀሙ ማድረግ ብሎም እውቅና መስጠት ነው›› ብለዋል፡፡

የሥርዓተ ምሕዳር ዋጋ ትመናና ክፍያ ለማስተዋወቅ በሃዋሳ ሐይቅ ላይ ጥናት መደረጉም ጠቁመዋል፡፡ የሥርዓተ ምሕዳር ግልጋሎት ዋጋ ትመና ሥርዓትን ተግባራዊ ለማድረግ ሁሉም ባለድርሻ አካላት በቅንጅት መሥራትና ለጉዳዩም ልዩ ትኩረት መስጠት እንዳለበትም አስገንዝበዋል፡፡

# አስተማማኝ የአየር ንብረት መረጃን የማጠናከር ሥራ እየተሠራ ነው

**ሳሙኤል ወንደሰን**




አዲስ አበባ፡- በመረጃ ላይ የተመሠረተ ውሳኔ እንዲሰጥ የሚያስችል አስተማማኝና ተደራሽ የአየር ንብረት መረጃን ለማጠናከር እየተሠራ እንደሆነ የኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት ገለጸ።

የኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር አቶ ፈጠነ ተሾመ 69ኛው የአፍሪካ ቀንድ የአየር ንብረት ትንበያ ፎረም ትናንት በአዲስ አበባ ሲካሄድ እንደተናገሩት፤ ኢንስቲትዩቱ የተሻለና በመረጃ ላይ የተመሠረተ ውሳኔ እንዲሰጥ የሚያስችል አስተማማኝና ተደራሽ የአየር ንብረት መረጃን ለማጠናከር እየተሠራ ነው።

ለዚህም ተደራሽነቱን በማስፋት፣ የክልል ማዕከላትን በማብቃት፣ መሣሪያዎችን በማዘመን እና የሠራተኞችን አቅም በማሳደግና በማጠናከር ላይ ይገኛል ብለዋል።

የአየር ንብረት ለውጥ መደበኛ ያልሆነ ዝናብ፣ ረጅም ድርቅ እና ከመጠን ያለፈ ዝናብ ያስከትላል። ይህም የእርሻ እና ሌሎች ዘርፎችን ተጋላጭ ያደርጋል ነው ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ፤ የአየር ንብረት ለውጥ አደጋዎችን ለመቀነስ እና ችግሮችን ወደ ዕድሎች ለመቀየር ወቅታዊና ተደራሽ የሆነ የአየር ንብረት መረጃ አስፈላጊ መሆኑን ተናግረዋል።

ኢንስቲትዩቱ በተለያዩ ቋንቋዎች ለተጠቃሚዎች የአየር ሁኔታ ትንበያን ወቅቱ የማሰራጨት ተግባራትን እያከናወነ እንደሚገኝም ገልፀዋል።

በይነ መንግሥታት የአየር ንብረት ትንበያ እና አፕሊኬሽንስ ማዕከል (ICPAC) ኃላፊ አብዲ ፊዳር (ዶ/ር) በበኩላቸው የአፍሪካ ቀንድ ለአየር ንብረት ለውጥ በጣም የተጋለጠ ነው። በዚህም ተደጋጋሚ ድርቅ፣ ጎርፍ እና ሌሎች አስከፊ የአየር ሁኔታ ክስተቶች ይስተዋላሉ ብለዋል።

እነዚህ ክስተቶች እንደ ግብርና፣ የውሃ ሃብትና ጤና ባሉ ቁልፍ ማኅበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ዘርፎች ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ እንዳላቸው ጠቁመው፤ አስተማማኝ እና ወቅታዊ የአየር ንብረት መረጃ በእነዚህ ዘርፎች ውጤታማ እቅድ ለማውጣት እና ውሳኔ ለመስጠት ወሳኝ መሆኑን ገልፀዋል። በአየር ንብረት ጉዳዮች ላይም ትብብርን ማጠናከር እንደሚገባም አንስተዋል፡፡

በውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር በሚኒስትር ዴኤታ ማዕረግ የሚኒስትሩ አማካሪ አቶ ሞቱማ መቃሳ በበኩላቸው፤ ኢትዮጵያ የአየር ንብረት አገልግሎትን ለማስፋፋት እና በቅድመ ማስጠንቀቂያ መረጃ ውጤታማ ውሳኔዎችን ለማሳለፍ ከሁሉም ባለድርሻ አካላት ጋር ለመተባበር ሙሉ በሙሉ ቁርጠኛ ነች ብለዋል።

በፎረሙ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አቅም ለመገንባት በመተግበር ላይ ያሉ ስትራቴጂዎች እና የተገኙ ውጤቶች ላይ የተመለከተ ውይይት እንደሚካሄድ ይጠበቃል። በፎረሙ የዘርፉ ተመራማሪዎች፣ ፖሊሲ አውጪዎችና የልማት አጋሮች ተገኝተዋል።

“የአየር ንብረት አገልግሎት፤ የቅድመ ማስጠንቀቂያ ክፍተቶችን በጋራ ለመሙላት” በሚል መሪ ሃሳብ በአዲስ አበባ የሚካሄደውን ፎረም የምስራቅ አፍሪካ የልማት በይነ መንግሥታት ባለሥልጣን (ኢጋድ) የአየር ንብረት ትንበያ እና የመተግበሪያ ማዕከል ከልማት አጋሮች ጋር በመተባበር ያዘጋጁት መሆኑ ተገልጿል።

# የተቀናጀ ውሃ ሀብት አስተዳደር ሥርዓትን ለማስፈን እየተሠራ ነው

**ኢያሱ መሰለ**

አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ የተቀናጀ የውሃ ሀብት አስተዳደር ሥርዓትን ማስፈን የሚያስችል የሕግ ማሕቀፍ ተግባራዊ ለማድረግ እየተሠራ መሆኑን የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር በትናንትናው እለት የተቀናጀ ውሃ ሀብት አስተዳደር ማስፈጸሚያ የተፋሰሶች ከፍተኛ ምክር ቤትን ለማቋቋም የተዘጋጀውን ረቂቅ አዋጅ አስመልክቶ ለውሃ፣ መስኖ፣ ቆላማ አካባቢ እና አካባቢ ልማት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ እንዲሁም ለባለድርሻ አካላት ማብራሪያ ሰጥቷል፡፡

በውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር የተቀናጀ ውሃ ሀብት አስተዳደር መሪ ሥራ አስፈጻሚ አቶ ደበበ ደፈርሶ ረቂቅ አዋጁን አስመልክተው ሲያብራሩ፤ በከፍተኛ አመራር ደረጃ አግባብነት ያላቸውን አካላት በማሳተፍ የተቀናጀ ውሃ ሀብት አስተዳደርን በተፋሰስ ደረጃ ተግባራዊ ማድረግ እና ስትራቴጂያዊ አመራር መስጠት አስፈልጓል፡፡

ውሃ የመላ ሀገሪቱ ዜጎች የጋራ ሀብት በመሆኑ በአመራር፣ በአስተዳደር፣ በጊዜ ሰሌዳ፣ በበጀት የተቀናጀ እና የተናበበ የከፍተኛ አመራር ውሳኔ የሚያስፈልገው መሆኑን ጠቁመው ለዚህም መንግሥት ለተቀናጀ ውሃ ሀብት አስተዳደር ከፍተኛ ትኩረት መስጠቱን ተናግረዋል፡፡

የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ፣ አረንጓዴ ዐሻራ፣ ፅዱ ኢትዮጵያ፣ ግድቤን በደጄና መሰል ትልልቅ ሀገራዊ ፕሮጀክቶች ከውሃ ጋር የተገናኙ እንደሆኑ ጠቅሰው፤ በውሃ ሀብት ላይ የጋራ እቅድ፣ የተናበበ አተገባበር፣ ጠንካራ ክትትልና ግምገማ ማድረግ ያስፈልጋል ብለዋል፡፡

በክልሎች ወይም በዘርፎች መካከል የሚከናወኑ ሀገራዊ ፋይዳ ያላቸው የልማት ፕሮጀክቶች ውጤታማነታቸውና ዘላቂነታቸውን የሚረጋገጠው የተቀናጀ የውሃ ሀብት አስተዳደር ሥርዓት ሲኖር እንደሆነ ተናግረዋል፡፡

የአየር ንብረት ለውጥን መቋቋም፣ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚን መገንባት፣ ዘላቂ ልማትን ማስፋፋት፣ የተፈጥሮ ሥነ-ምሕዳርን መጠበቅ፣ የውሃ ሀብት መጠንንና ጥራትን ማረጋገጥ የሚቻለው፤ የተቀናጀ የውሃ ሀብት አስተዳደርን መተግበር ሲቻል እንደሆነ ገልጸዋል፣ ይህም የኢትዮጵያ የውሃ ሀብት አስተዳደር ፖሊሲን ሙሉ ለሙሉ ተፈጻሚ ለማድረግ የሚያስችል እንደሆነም ተናግረዋል፡፡

በውይይቱ የተሳተፉ ባለድርሻ አካላት ከቀረበው ማብራሪያ በኋላ፤ ረቂቅ አዋጁ ለዝናብ ውሃ ለምን ትኩረት አልሰጠም? ረቂቅ አዋጁ የውሃ ብክለትን እንዴት መታደግ እንደሚቻል ያስቀመጠው ነገር የለም? ከውሃ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸው አንዳንድ ተቋማት ለምን እንዲካተቱ አልተደረገም? ረቂቅ አዋጁ በክልሎች መካከል ለሚነሱ ቅሬታዎች ምን አይነት መፍትሔ ይሰጣል? መጤ አረሞች በውሃ ሀብት ላይ እያደረሱ ያለውን አደጋ እንዴት ለመከላከል ታስቧል? የሚሉት ጥያቄዎች ከተሳታፊዎች ተነስተዋል፡፡

የውሃና ኢነርጂ ሚኒስትር ሀብታሙ ኢተፋ (ዶ/ር) እና የተቋሙ ከፍተኛ አመራሮች በሰጡት ምላሽ፤ በውሃ የመጠቀም ፍላጎት ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ መምጣቱንና የሕዝብ ቁጥር መጨመር የውሃ ተፈላጊነትን እያሳደገው እንደሚገኝ አስረድተዋል፤ በውሃ ምክንያት ግጭት እንዳይኖር ከአሁኑ መፍትሔ ማስቀመጥ አስፈልጓልም ብለዋል፡፡

ሰነዱ ከውሃ ጋር ግንኙነት ያላቸው የተለያዩ መሥሪያ ቤቶችን በማሳተፍ መግባባት ላይ የተመሠረተ ቅንጅታዊ አሠራር እንዲኖር የሚያስችል በመሆኑ በርካታ ችግሮችን እንደሚፈታ ጠቅሰዋል፡፡

ከተለያዩ መሥሪያ ቤቶች የተውጣጡ አካላትን ያሳተፈ ከፍተኛ ምክር ቤት ማቋቋም ያስፈለገውም ችግሮች በምክክር እንዲፈቱ የሚያደርግ ድንጋጌ ለማስቀመጥ ነው ብለዋል፤ በረቂቅ አዋጁ ላይ የተሰጡ አስተያየቶችን መሠረት በማድረግ በአንዳንዶቹ ላይ እርማት የሚደረግ ስለመሆኑም ጠቅሰዋል፡፡

የውሃ፣ መስኖ፣ ቆላማ አካባቢ እና አካባቢ ልማት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ወይዘሮ ፈቲያ አሕመድ በበኩላቸው፤ ቋሚ ኮሚቴው በውይይቱ ወቅት የተነሱ እና በቃለ ጉባኤው የተያዙ ጥያቄዎችን በጥልቀት ተመልክቶ መልስ እንዲያገኙ በማድረግ ረቂቅ አዋጁ እንዲዳብር ያደርጋል ብለዋል፡፡

# በዓለም አቀፍ የስፖርት ተቋማት የኢትዮጵያውያን ሚና ሲፈተሽ



ብርሃን ፈይሳ

**ዜና ትንታኔ**

ኢትዮጵያ በአሕጉር አቀፍ የስፖርት ማኅበራት ምሥረታ የቀደመ ታሪክ ያላት ሀገር ነች፡፡ እንደ ይድነቃቸው ተሰማ ያሉ የስፖርቱ ዓለም ታላላቅ ሰዎች በአፍሪካ እግር ኳስና ኦሊምፒክ ባበረከቱት አስተዋፅዖ «የአፍሪካ ስፖርት አባት» እስከመሰኘት ደርሰዋል፡፡ አቶ ፍቅሩ ኪዳኔም እስከ ዓለም አቀፉ ኦሊምፒክ ኮሚቴ የዘለቀ ሚናቸው በስኬት ሊጠቀስ ይችላል። ባለፉት ዓመታት ደግሞ ወይዘሮ ዳግማዊት ግርማይ በዓለም ኦሊምፒክ የሥራ አስፈጻሚ አባልነት የሚያደርጉት እንቅስቃሴ ተጠቃሽ መሆኑን የዘርፉ ምሁራን ይጠቅሳሉ፡፡

እነዚህ የስፖርት አመራሮች በዓለም አቀፍ ደረጃ ያላቸው ውክልና በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ለኢትዮጵያ ስፖርት የሚያበረክተው አስተዋፅዖ ቀላል አይደለም። ኢትዮጵያውያን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በአሕጉር አቀፍ የስፖርት ተቋማት ውስጥ ከመወከል አልፈው የመሪነት ሚና ያገኙበት ዕድል ተፈጥሯል። ይሁን እንጂ እንዳለፉት ዘመናት የስፖርት መሪዎች በዓለምም ይሁን በሀገር ውስጥ ስፖርት ያላቸው ሚና እምብዛም ጎልቶ አይታይም፡፡

ይሁን እንጂ በቅርቡ በአፍሪካ ቦክስ ኮንፌዴሬሽን ፕሬዚዳንትነት የተመረጡት አቶ ኢያሱ ወሰን የአሕጉራዊው ኮንፌዴሬሽን ጽሕፈት ቤት አዲስ አበባ ላይ እንዲሆን ከማድረግ ባሻገር የኢትዮጵያን የቦክስ ስፖርት ለማነቃቃት ጥረት እያደረጉ ይገኛሉ። አቶ ኢያሱ የአፍሪካን የቦክስ ስፖርት ለመምራት በመቻላቸው ኢትዮጵያ እንደሀገር በስፖርቱ ያላት ተፅዕኖ ከፍ ማለቱን የአፍሪካ ቦክስ ኮንፌዴሬሽን የጽሕፈት ቤት ኃላፊ አቶ ዮሐንስ ብርሃኔ ይናገራሉ፡፡

እንደ ጽሕፈት ቤት ኃላፊው ገለፃ፣ በአሕጉር አቀፉ ኮንፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት መሆን በዓለም አቀፉ ማኅበር የቦርድ አባልነት ዕድልን ስለሚያስገኝ ለሌሎች ብሔራዊ የስፖርት ማኅበራት መነቃቃት በመፍጠር ረገድ አሁን በቦክስ ስፖርት የተገኘው ዕድል አርዓያ ነው።

በሥልጠናዎች ላይ ኢትዮጵያውያን ባለሙያዎች ቅድሚያ እንዲያገኙ እንዲሁም ከማኅበራቱ በሚገኙ ዕድሎች የውድድር ቁሳቁስ ድጋፍ በማድረግም ኢትዮጵያ እየተጠቀመች ነው፡፡ በቅርቡ በአዲስ አበባ ለመጀመሪያ ጊዜ የተካሄደውን አሕጉር አቀፍ ውድድርና ጉባኤ ዓይነት በማምጣትም ከኢትዮጵያውያን ስፖርተኞች በተጨማሪ ሀገር በተለያየ መንገድ እንድትጠቀም ማድረግ ተችሏል።

የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ጽሕፈት ቤት ኃላፊ አቶ ዮሐንስ እንግዳ በበኩላቸው፤ በዓለምና አሕጉር አቀፍ የስፖርት ተቋማት ውስጥ ውክልና ማግኘት በርካታ ጠቀሜታ እንዳለው ያስረዳሉ።

ዓለም አቀፍና አሕጉር አቀፍ ውሳኔዎች ሲተላለፉ የሀገርን ጥቅም ለማስጠበቅም ጥቅም አለው ይላሉ። ዓለም አቀፍና አሕጉር አቀፍ ውድድሮችን፣ ሥልጠናና ጉባዔዎችን ወደ ሀገር ውስጥ ለማምጣትም ትልቅ አስተዋፅዖ አለው ባይ ናቸው።

"በአትሌቲክስ ስፖርት ኬንያ ያላት ውክልና ከጊዜ ወደ ጊዜ እየሰፋ በዓለም አትሌቲክስ የምክትል ፕሬዚዳንትነት ደረጃ ደርሳለች፡፡ በዚህም እንደ ሀገር ዘርፈ ብዙ ጥቅሞችን ታገኛለች፤ የውድድር ዕድሎች፣ የሥልጠና ማዕከላት መቀመጫ በመሆን፣ በባለሙያዎች ሥልጠና የተሻለ ዕድል በማግኘት፣ ኬንያውያን አትሌቶች ላይ በሚወሰኑ ውሳኔዎች ላይም ተፅዕኖ አላቸው።" በማለት አቶ ዮሐንስ ጎረቤት ሀገር ኬንያን በምሳሌነት ያነሳሉ። ኢትዮጵያም መሰል ሚና ቢኖራት የዓለም አትሌቲክስ የረጅም ርቀት የመም ውድድሮችን ለመሰረዝ ያለውን ሃሳብ ለማስቀየር አቅም እንደሚኖራት ማሳያ አድርገው አብራርተዋል፡፡

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የስፖርት ሳይንስ ትምህርት ክፍል መምህር ዘሩ በቀለ (ዶ/ር) በበኩላቸው፣ ዓለም አቀፍ ልምዶችን ወደ ሀገር በማምጣት የዕውቀት ሽግግር ለማግኘት የስፖርት አመራሮች በዓለምና አሕጉር አቀፍ የስፖርት ተቋማት መወከላቸው ቀላል የማይባል ሚና እንዳለው ያስረዳሉ። አክለውም፣ ስፖርትን እንደ ንግድ ለመጠቀም፣ በቀጣይ የሚኖረውን የዓለም የስፖርት አቅጣጫን ከወዲሁ ለመተንበይ እንዲሁም እንደ ሀገር የሚንቀሳቀሱ የስፖርት ተቋማት የትኩረት አቅጣጫ ምን መሆን እንዳለበት ውሳኔዎች ላይ ሀገር ሚና እንዲኖራት ይረዳል በማለትም ያብራራሉ፡፡

በአፍሪካና በዓለም ደረጃ ድንቅ ታሪክ ማጻፍ የቻሉ የስፖርት አመራሮችን ሰዎችን ያፈራችው ኢትዮጵያ አሁን ላይ በአሕጉርም ሆነ በዓለም አቀፍ የስፖርት ተቋማት ያሏት አመራሮች እጅግ ጥቂት ናቸው። ለዚህ አቅም ያለው ሰው አለመገኘቱን ምክንያት የሚያደርጉ ብዙዎች ቢሆኑም፣ የስፖርት ሳይንስ መምህሩ ዘሩ (ዶ/ር) ግን በዚህ ሃሳብ አይስማሙም። ለዚህም እነ ይድነቃቸው ተሰማ በዓለም አቀፍ ደረጃ ጎልተው በወጡበት ወቅት ኢትዮጵያ እንደሀገር የነበራት ፖለቲካዊ ተፅዕኖ፣ የአፍሪካ አንድነት ድርጅትን በማቋቋም እንዲሁም የአፓርታይድ ሥርዓትን ለማስቆም በሚደረገው እንቅስቃሴ የነበራት አበርክቶ፣ በአሕጉር አቀፍ ደረጃ በብዙ መንገድ የነበራትን ተሰሚነት የጎላ የነበረ በመሆኑ በስፖርቱም ኢትዮጵያውያን በቀላሉ አሕጉራዊም ሆነ ዓለም አቀፋዊ ተቋማት ውስጥ ለመግባት ቀላል ነበር የሚል መከራከሪያ አላቸው፡፡ ኢትዮጵያ አሕጉር አቀፍ የስፖርት ማኅበራትን በማቋቋም ረገድ የነበራት የመሪነት ሚናም የራሱ አስተዋፅዖ ነበረው ሲሉም ያክላሉ። ከዚያ በኋላ ባሉት ዓመታት ሀገራት በብዙ መልኩ ሲለወጡ ኢትዮጵያ የነበራትና እንቅስቃሴ ግን ማስቀጠል አልተቻለም ባይ ናቸው።

እንደ ዘሩ (ዶ/ር) ገለፃ፣ አሁን ላይ በዓለምና አሕጉር አቀፍ የስፖርት ተቋማት ውስጥ ለመግባት በርካታ መስፈርቶች ያሉ ከመሆኑም በላይ በሀገር ውስጥ ያለው ስፖርታዊ እንቅስቃሴም ወሳኝነት አለው። በአንድ ስፖርት በምሥራቅ አፍሪካ ጠንካራ ሆኖ ሳይገኙ የቀጣናውን ማኅበር መምራት ከባድ ነው፡፡ ይህም ብቻ ሳይሆን በስትራቴጂ ተፎካካሪ ሆኖ መገኘት የግድ ነው። በዚህ ረገድ የኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ የሚያሳየው ብሔራዊ የስፖርት ተቋማት ላይ በሥራ አስፈጻሚነት የሚወከሉ ሰዎች ወደ ኃላፊነት የሚመጡበትን መንገድ መፈተሽ ያስፈልጋል ይላሉ። ለዚህም የኢትዮጵያን ስፖርት የሚመሩ አብዛኞቹ ሰዎች የቋንቋ፣ የስትራቴጂያዊና አስተዳደራዊ ጉዳዮችን በተመለከተ አሕጉርና ዓለም አቀፍ መድረኮች ላይ በሚሳተፉባቸው በጉባኤዎች ሃሳብን የመግለጽ እንዲሁም ጎልቶ የመውጣት ችግር መኖሩን ምክንያት አድርገው ይጠቅሳሉ።

ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ ከሆነችባቸው ስፖርቶች አትሌቲክስ ግንባር ቀደም ነው። እንደ ኢትዮጵያውያን አትሌቶች ውጤታማነት ግን የአመራሩ ዓለም አቀፍ ተሳትፎ ማደግ አልቻለም። ኬንያ በአንፃሩ የተሻለ ደረጃ ላይ ትገኛለች። ይህ በሌሎችም ስፖርቶች ተመሳሳይ ነው።

ኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ጽሕፈት ቤት ኃላፊው አቶ ዮሐንስ፣ የኢትዮጵያን ስፖርት ለመምራት ወደኃላፊነት የሚመጡ ሰዎች ያላቸው ዕውቀት እና የግንኙነት መስመር መለያየት በአሕጉርም ሆነ ዓለም አቀፍ ስፖርት ላይ የጎላ ሚና ኖሯቸው እንዳይታዩ ማድረጉን ያምናሉ። ለአብነት የአፍሪካ አትሌቲክስን በመምራት ላይ ያሉት ካሜሮናዊም ሆኑ የቀድሞው ሴኔጋላዊ ፕሬዚዳንት ሀገራቸው በስፖርቱ የተለየ ውጤታማነት ኖሯቸው አይደለም ይላሉ፡፡ ነገር ግን ዕድሎቻቸውን በአግባቡ በመጠቀማቸው በአሕጉር አቀፍ ደረጃ ስፖርቱን ለመምራት በቅተዋል።

እንደ አቶ ዮሐንስ ሃሳብ፣ በሀገር አቀፍ የስፖርት ተቋማት ወንበር ማግኘት ብቻውንም ጠቃሚ ሊሆን አይችልም። ወደላይ የማስቀጠልና ተጠቃሚ የመሆን ጉዳይም ጥያቄ ውስጥ ይገባል፡፡ በመሆኑም በሀገር ደረጃ ስፖርቱን ለመምራት የሚመጡ ሰዎች ካላቸው ተሰሚነት፣ ተፅዕኖ ፈጣሪነትና ከአቅም አንጻር ተገቢ መሆን አለባቸው። ክልሎችም ለምርጫ የሚያቀርቧቸውን ተወካዮች ተገቢነት ማጤን አለባቸው ይላሉ።

የአፍሪካ ቦክስ ኮንፌዴሬሽን ጽሕፈት ቤት ኃላፊ አቶ ዮሐንስ፣ በአሕጉርና ዓለም አቀፍ የስፖርት ተቋማት ውክልናን ለማግኘት በቅድሚያ በሀገር ውስጥ የሚታይ ሥራ ማከናወን እንዲሁም ራስን ማስተዋወቅ እንደሚያስፈልግ ይናገራሉ።

ዕድሉ በቀላሉ ስለማይገኝም ኢትዮጵያውያን የስፖርት አመራሮች ከጊዜ፣ ጉልበትና ገንዘብ አንፃር ተገቢውን ዋጋ መክፈል ይጠበቅባቸዋል ሲሉም ይመክራሉ። መንግሥትም የራሱን እገዛ ማድረግ እንዳለበትም አክለዋል።

የስፖርት መምህሩ ዘሩ (ዶ/ር) በበኩላቸው፣ የኢትዮጵያን ስፖርት የሚመሩ ሰዎች ወደ አሕጉርና ዓለም አቀፍ ደረጃ ከማማተራቸው በፊት በየክልሉ የሚታይ ሥራ በማከናወን፣ በሃገር አቀፍ ደረጃ ጎልተው በመውጣት መንግሥትም አምኖባቸው እንዲደግፋቸው ማድረግ አለባቸው ይላሉ።

ለዚህም ስፖርቱን የሚመራው የባሕልና ስፖርት ሚኒስቴር ክልሎች የሀገሪቱን ስፖርት እንዲመሩ ዕጩ አድርገው የሚወክሏቸው ሰዎችን ተጨባጭ ሥራ መሥራታቸውን የሚያረጋግጥ የውክልና እና ምርጫ ሥርዓትን ማዘጋጀት እንደሚገባ ምክረ ሀሳብ ሰጥተዋል።

# በስድስት ወራት 204 ሺህ ቶን ቡና ለውጭ ገበያ ቀረበ

## - ወደ ጀርመን ከተላከው ቡና ብቻ 161 ሚሊዮን ዶላር ገቢ ተገኝቷል



ሞገስ ፀጋዬ

አዲስ አበባ፡- ባለፉት ስድስት ወራት 204 ሺህ ቶን ቡና ለውጭ ገበያ በማቅረብ 908 ሚሊዮን ዶላር ገቢ መገኘቱን የቡናና ሻይ ባለሥልጣን አስታወቀ፡፡

የባለሥልጣኑ ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ሻፊ ዑመር ባለሥልጣኑ የስድስት ወር አፈጻጸም አስመልክቶ ትናንት በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ እንዳሉት፤ ከ2014 በጀት ዓመት ወዲህ ከቡና የሚገኘው ገቢ በፍጥነት እያደገ መጥቷል፡፡ በ2017 በጀት ዓመት የቡና ምርትና ጥራትን በማሳደግ ከ400 ሺህ ቶን በላይ ቡና ለውጭ ገበያ በማቅረብ ሁለት ቢሊዮን ዶላር ገቢ ለማግኘት እቅድ ተይዞ እየተሠራ ነው፡፡

በስድስት ወራት 133 ሺህ ቶን ቡና በመላክ 714 ሚሊዮን ዶላር ገቢ ለማግኘት እቅድ መያዙን የገለጹት፤ አቶ ሻፊ፡- ባለፉት ስድስት ወራት በመጠን ወደ 204 ሺህ ቶን ቡና ለውጭ ገበያ በማቅረብ 908 ሚሊዮን ዶላር

ወደ 4ኛ ገጽ ዞሯል

# በሰሜኑ ጦርነት የተጎዱ የ46 አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መልሶ ግንባታ ተጠናቀቀ

**ሰላማዊት ውቤ**

አዲስ አበባ፡- በሀገራችን የሰሜኑ ክፍል በነበረው ግጭት የተጎዱትን 50 የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መልሶ ግንባታ 46ቱን ማጠናቀቁንና ለተማሪ ቅበላ ዝግጁ ማድረጉን ትምህርት ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

በትምህርት ሚኒስቴር የትምህርት ቤቶች ግንባታ ፕሮጀክት ጽሕፈት ቤት ሥራ አስኪያጅ ከተማ መስቀላ (ዶ/ር) ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ እንደገለጹት፤ ከ50ው የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የ46ቱ ግንባታ ሥራ ተጠናቋል፡፡ በዓለም ባንክና ከሌሎች ለጋሽ ድርጅቶች በተገኘ የ25 ሚሊዮን ዶላር የግንባታው ወጪ መሸፈኑን ገልጸዋል፡፡

ባለፉት ሁለት ዓመታት 50 የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን ለመገንባት ታቅዶ 46ቱ መጠናቀቃቸውን ገልጸው፤ አራቱ በግንባታ ሂደት ላይ መሆናቸውን እና ከተጠናቀቁት ውስጥ አብዛኛዎቹ አገልግሎት መስጠት መጀመራቸውን ከተማ መስቀላ (ዶ/ር) አስረድተዋል፡፡

በግንባታ ሂደት ላይ ያሉትን ጨምሮ ሙሉ በሙሉ ትምህርት ቤቶቹ አገልግሎት ወደ መስጠት ሲገቡ ከ22 ሺህ በላይ የሚሆኑ ተማሪዎችን የሚያስተናግዱ እንደሆነም ገልጸዋል፡፡

በአማራ ክልል ለመገንባት ታቅደው የነበሩት በጦርነቱ የተጎዱ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ግንባታ ሙሉ ለሙሉ መጠናቀቁን አብዛኞቹም ተማሪ ተቀብለው ወደ ማስተማር መግባታቸውን አመልክተዋል፡፡

በጦርነት ከተጎዱት 10 የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል የአንዱ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ግንባታ በደሴ ከተማ መጀመሩን እና የግንባታ ሂደት ላይ መሆኑን ጠቁመው፤ የዘጠኙ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የዲዛይን እና የተቋራጭ መረጣ እየተካሄደ ይገኛል ብለዋል፡፡

የትምህርት ጥራት ችግር በትምህርት ዘርፍ አንድ ቁልፍ ጉዳይ መሆኑን ያነሱት ሥራ አስኪያጁ፤ ለዚህም አንዱ ምክንያት የትምህርት ቤቶች መሠረተ ልማት በበቂ ደረጃ አለመሟላት ነው ብለዋል፡፡

የትምህርት ጥራትን ለማረጋገጥ ደረጃቸውን የጠበቁ ትምህርት ቤቶችን የመገንባት እና በቂ ግብዓት እንዲኖራቸው የማድረግ ሥራዎችን ትምህርት ሚኒስቴር በትኩረት እየሠራ እንደሆነ አመልክተዋል፡፡

ሞዴል ትምህርት ቤቶችን በመገንባት ረገድ ከመንግሥት የተበጀተ በጀት አለመኖሩን ጠቅሰው፤ ከዓለም ባንክ እና ከተለያዩ ርዳታ ሰጪ ድርጅቶች በሚገኝ ገንዘብ ትምህርት ቤቶቹን ለመገንባት ጥረት እየተደረገ እንዳለ ገልጸዋል፡፡ ለአብነት ያህልም ሞዴል ትምህርት ቤቶችን ከመገንባት አንፃር በዋናነት ሰዎች ለሰዎች የተሰኘው ድርጅት ድጋፍ እያደረገ እንደሚገኝም ጠቅሰዋል፡፡

ትምህርት ሚኒስቴር ለመገንባት በዕቅድ ይዟቸው ከነበሩ 50 ሞዴል አዳሪ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ሰዎች ለሰዎች ድርጅት 16ቱን ለመገንባት ቃል መግባቱን አመላክተዋል። እስከ አሁንም የስድስት ትምህርት ቤቶችን ግንባታ እንዳጠናቀቀ ተናግረዋል፡፡

በመጀመሪያው ምዕራፍ በእቅድ ከተያዙት 50 ትምህርት ቤቶች 13 ትምህርት ቤቶች መገንባታቸውን ጠቅሰዋል፡፡

ቀሪዎቹን ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች እንዲገነቧቸው ስምምነት መደረጉንና አንዳንዶቹም በግንባታ ሂደት ላይ ያሉ መሆኑን የትምህርት ቤቶች ግንባታ ፕሮጀክት ጽሕፈት ቤት ሥራ አስኪያጅ ከተማ መስቀላ (ዶ/ር) ገልጸዋል፡፡

# በኢትዮጵያ በትራክተር የማረስ ምጣኔ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ሥራው ተመራጭ ሆኗል ብለዋል።

የግብርና መካናይዜሽን ትልቁ ሥራው ቴክኖሎጂን እንዲስፋፋ እና አርሶ አደሩ ጋር ተደራሽ እንዲሆን ማድረግ መሆኑን ጠቁመው፣ የግብርናውን ዘርፍ ለማዘመን የግብርና መካናይዜሽን አገልግሎት አሠራር ላይ በትኩረት እየተሠራ መሆኑን ተናግረዋል።

በቴክኖሎጂ በመታገዝ የግብርና ሥራው በተከናወነባቸው አካባቢዎች ምርታማነት እየጨመረ መሆኑን የገለፁት አቶ እሸቱ፤ በ2016/17 የምርት ዘመን አርሶ አደሩ ምርቱን በግብርና ቴክኖሎጂዎች ታግዞ እየሰበሰበ ነው ብለዋል።

በግብርና ሚኒስቴር የ10 ዓመቱ ስትራቴጂክ እቅድ አሁን ያለውን 20 ሺህ ገደማ ትራክተር ወደ 65 ሺህ ለማሳደግ ታቅዶ እንቅስቃሴ እየተደረገ መሆኑንም ጠቁመዋል።

ኮምባይነር ከቀረጥ ነፃ ከመሆኑ በፊት በቁጥር ከ500 የማይበልጥ እንደነበር አውስተው፣ አሁን ላይ ሁለት ሺህ 700 መድረሱንና በቀጣይ 15 ሺህ ለማድረስ ታቅዷል። እንዲሁም አርሶ አደሩም በቂ ግንዛቤ እንዲኖረው ለማድረግ እየተሠራ ነው ብለዋል።

በግብርና መካናይዜሽን የአነስተኛ አርሶ አደር ምርትና ምርታማነትን በመጨመር ጥራትን በማሻሻል እንዲሁም የቅድመ እና ድህረ ምርት ብክነትን ለመቀነስ ሲሠራ መቆየቱን አንስተው፤ በዚህም ባለፉት ስድስት ዓመታት የግብርና መካናይዜሽን ቴክኖሎጂዎች አቅርቦት አገልግሎት አሰጣጡን አሻሽሏል ነው ያሉት።

የግብርና ማሽነሪዎች ከቀረጥ ነፃ እንዲሆኑ መፈቀዱ ለዘርፉ መዘመን የራሱ አስተዋፅዖ አድርጓል ያሉት አቶ እሸቱ፤ መንግሥት ከ2012 ዓ.ም ጀምሮ ማሽነሪዎቹ ከቀረጥ ነፃ እንዲገቡ ከፈቀደ ወዲህ በርካታ ቴክኖሎጂዎች ገብተዋል፤ እየገቡም ይገኛሉ። በዓይነትና በቁጥር በርካታ የሆኑ ማሽነሪዎች ሀገር ውስጥ በመግባታቸው በርካታ የመካናይዜሽን አገልግሎት ሰጪዎች እየተፈጠሩ እና የኪራይ አገልግሎት የሚሰጡ ባለሀብቶች ከአርሶ አደሩ ጋር እየተሳተፉ ነው ብለዋል።

ከአምስት ዓመት በፊት አምስት ሺህ ያህል ትራክተር እንደነበር አስታውሰው በአሁኑ ጊዜ ወደ 20 ሺህ ትራክተር ማሳደግ ተችሏል። የማሽነሪ ዋጋ ከቀረጥ ነፃ እንዲገባ የተደረገበት ሁኔታ የፍላጎት መጨመር መፈጠሩንና አርሶ አደሩ ቴክኖሎጂን በስፋት እንዲጠቀም ማስቻሉን ገልፀዋል።

በኢትዮጵያ የመጀመሪያ የሆነው በኮሪያ መንግሥት የገንዘብ ድጋፍ የተገነባው የግብርና መካናይዜሽን የልህቀት ማዕከል ተጠናቅቆ ማሽነሪዎችን እያስገባ መሆኑን ጠቁመው፣ የጥገና እና የሥልጠና ማዕከል ሆኖ አገልግሎት ለመስጠት አስተዋፅዖ እንደሚኖረው አመልክተዋል።

በኢትዮጵያ በትራክተር ማረስ እና የግብርና መካናይዜሽንን መጠቀም በኦሮሚያ ክልል ባሌ እና አርሲ አካባቢ ቀደም ብሎ ሥራ ላይ የዋለ መሆኑን አስታውሰው፣ አማራ፣ ሶማሌ እና አፋር ጨምሮ ወደ ሁሉም ክልሎች ሰፊ እንቅስቃሴዎች እንዳሉ ጠቁመዋል።

በየክልሉ 10 ያህል የእርሻ መካናይዜሽን አገልግሎት የሚሰጡ ማዕከላት መኖራቸውን ጠቁመው፤ ከዩኒየኖች ጋር በመሆን ማሽነሪዎችን መግዛት የማይችሉ አርሶ አደሮች በኪራይ እንዲያገኙ እየተደረገ ነው። አቅም ያላቸው ባለሀብቶች ገዝተው የማከራየት አገልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ ብለዋል።

አጨዳ ላይ ምርት ቀድሞ በሚደርስባቸው ቆላማ አካባቢዎች አገልግሎት ከሰጡ በኋላም ወደ ሌላ አካባቢዎች በመሄድ አገልግሎት እየሰጡ መሆኑንም ጠቁመዋል።

የኢትዮጵያ ልማት ባንክ የግብርና መካናይዜሽንን ከማስፋት አኳያ አገልግሎት አቅራቢ መሆኑን ጠቁመው፤ በሊዝ ፋይናንስ ችግር እየተቀረፈ ነው ብለዋል።

አሁን ላይ በትራክተር የማረስ ሁኔታው አምስት ሚሊዮን ሄክታር ደርሷል ነገር ግን ይህ በቂ ባለመሆኑ በቀጣይ 10 ዓመቱ ስትራቴጂክ እቅድ ወደ 11 ሚሊዮን ሄክታር በትራክተር ለማረስ እንደሚሠራ አመላክተዋል።

በመኸር ወቅቱ ከበጋ መስኖ ወጪ አምስት ሚሊዮን ሔክታር መሬት በትራክተር መታረሱን የግብርና ሚኒስቴር መግለፁ ይታወሳል።

# በስድስት ወራት 204 ሺህ ቶን ቡና...

ከ3ኛ ገጽ የዞረ

ገቢ መገኘቱን ተናግረዋል፡፡

በመጠን ከእቅዱ አንጻር የ153 በመቶ ብልጫ ያለው እንደሆነ ጠቁመው፤ በገቢም 127 በመቶ መፈጸም ተችሏል፡፡ ከገቢ አንጻር ከባለፈው ተመሳሳይ ዓመት ጋር ሲነጻጸር 337 ሚሊዮን ዶላር ብልጫ እንዳለው ገልጸዋል፡፡

ጠንክሮ በመሥራትና የነበሩ ችግሮችን መቅረፍ በመቻሉ በስድስት ወራት አመርቂ ውጤት ማግኘት መቻሉን አመልክተው፤ በ2017 በግማሽ ዓመት የተገኘው ውጤት ከ2013 ሙሉ ዓመት ጋር ሲነጻጸር እኩል እንደሆነ ጠቁመዋል፡፡ እንደ አቶ ሻፊ ገለጻ፤ ከጊዜ ወደ ጊዜ የቡና ገቢ እያደገ መጥቷል፡፡ የቡና አርሶ አደሮችን ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ ፈጣን እድገትን ለማስመዝገብ የሚያስችል ሥራ ቡና ላይ ተሠርቷል፡፡ ቀጣዩ ስድስት ወራት አዲስ ቡና የሚገባበት በመሆኑ ከፍተኛ የቡና ሽያጭ የሚፈጸምበት ነው፡፡

በስድስት ወር የተመዘገቡ ስኬቶችን ዳግም ለማስመዝገብ የቆዩ ኮንትራቶችን በመጠንና በዋጋ ማሻሻያ በማድረግ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ እንዲያስገቡ የማድረግ ሥራ ተሠርቷል ያሉት አቶ ሻፊ፤ የ53 ላኪዎች 56 ኮንትራቶችን በማሻሻል ሦስት ሺህ 993 ቶን ቡና ወደ ውጭ እንዲላክ በማድረግ 14 ሚሊዮን ዶላር ገቢ ማግኘት መቻሉን ነው የገለጹት፡

እንደ አቶ ሻፊ ገለጻ፤ በ90 ቀን ማለቅ ሲገባው የመጫኛ ጊዜ ያለፈባቸው ቡናዎችን ኮንትራቱን በማሻሻል ወደ ውጭ እንዲልኩ የተሠሩ ሥራዎች ለመጣው ውጤት ትልቅ አስተዋፅዖ አላቸው፡፡

ባለፉት ስድስት ወራት 141 ላኪዎች 717 ኮንትራቶችን በማሻሻል 21 ሺህ ቶን ቡና እንዲልኩ በማድረግ 99 ሚሊዮን ዶላር ገቢ አስገኝተዋል፡፡

አዲስ ገበያዎችን በማፈላለግ ገቢን የመጨመር ሥራ እየተሠራ መሆኑንም የገለጹት ምክትል ዳይሬክተሩ፤ 64 ለሚሆኑ ሀገሮች ቡና ይላካል፡፡ በስድስት ወር ከተገኘው ገቢ ውስጥ 10 ሀገራት በመጠንና በገቢ 76 በመቶ ድርሻ ይይዛሉ፡፡ ባለፉት ስድስት ወራት 39 ሺህ 137 ቶን ቡና ወደ ጀርመን በመላክ 161 ሚሊዮን ዶላር ገቢ ማግኘት መቻሉን ጠቅሰዋል፡፡

በስድስት ወራት ውስጥ ጆርዳን የኢትዮጵያን ቡና ከሚረከቡ አስር ሀገራት መካከል አንዷ ሆናለች ያሉት አቶ ሻፊ፤ በዚህም ከፍተኛ ውጤት እንዲመጣ የአቅራቢና ላኪ ትስስር እንዲጠናከር ማድረግ መቻሉን ገልጸዋል፡፡

# በስድስት ወራት...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

በፈጸሙ 18 የተቋሙ ሠራተኞች ላይ ሕጋዊና አስተዳደራዊ እርምጃ መወሰዱን ገልጸዋል።

ባለፉት 6 ወራት ከ2 ሚሊዮን 50 ሺህ በላይ የንግድና ምዝገባ ፈቃድ አገልግሎት መሰጠቱን አመልክተው፤ ካለፈው ዓመት 2 ነጥብ 4 ሚሊዮን ዓመታዊ አፈጻጸም አንፃር ሲታይ በጣም ከፍተኛ ነው ብለዋል።

በሲሚንቶ ግብይት ማሻሻያ የተረጋጋ አቅርቦትና ግብይት እንዲኖር በመደረጉ ዋጋው በግማሽ መቀነሱንም ሚኒስትሩ በማኅበራዊ ትስስር ገጻቸው ባጋሩት ጽሑፍ ጠቅሰዋል።

በጨው ግብይት ሪፎርምም በጥቂት ነጋዴዎች በሞኖፖሊ ተይዞ የነበረው ግብይት በፍትሐዊነት ለሁሉም ክፍት መደረጉን ጠቁመዋል፡፡

የጥራት መንደር ኢትዮጵያን በሚወክልና በሚያስደንቅ ደረጃ ለሀገር ኩራት ሆኖ መጠናቀቁም የግማሽ ዓመቱ ተጠቃሽ ክንውናችን ነው ሲሉ ጠቅሰዋል።

የዓለም የንግድ ድርጅት አባልነት ድርድር ተቋርጦ ከነበረበት ምዕራፍ በማውጣት ወደ ንቁ የድርድር ዓውድ መግባቱን ጠቅሰው፤ ለቀጣይ 5ኛ ዙር ድርድርም ብቃት ያላቸውን ሙያተኞችን በማደራጀት በቂ ዝግጅት እየተደረገ ነው ብለዋል።

ነዳጅ በሕገ-ወጥ መንገድ በማጓጓዝ የተሳተፉ ኩባንያዎች 116 ሚሊዮን ብር እንዲቀጡ መደረጉን አንስተው፤ ባለፉት 6 ወራት የነዳጅ ግብይትን ሥርዓት ለማስያዝ በተሠራ ሥራ በሕገ-ወጥ መንገድ ሲጓጓዝ የነበረ 325 ሺህ ሊትር ነዳጅ በቁጥጥር ስር መዋሉን አስታውቀዋል።

በድርጊቱ የተሳተፉ ኩባንያዎች 116 ሚሊዮን ብር እንዲቀጡ መደረጉንም የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስትሩ ካሣሁን ጎፌ (ዶ/ር) ገልጸዋል።

# “በዲጂታሉ ዓለም...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

የሚችል ነው ብለዋል፡፡

‹‹አሁን ባለንበት ዓለም ወደ ዲጂታል ከመግባት ውጭ ሌላ አማራጭ የለንም›› ያሉት አብዮት (ዶ/ር)፤ ዲጂታል ዓለም ውስጥ እንደመሆናችን ከዲጂታሉ ዓለም ለመጠቀም ዲጂታል ማንነት መሠረታዊ ጉዳይ ነው ብለዋል፡፡

ፋይዳ ወይም ዲጂታል መታወቂያን በተመለከተ አንደኛውና ዋናው ነገር በሀገራችንም ሆነ በዓለም ላይ የዲጂታል ማንነት ጉዳይ ተጠናክሮ የሚቀጥል እንጂ፤ ወደኋላ የሚመለስ እንዳይደለ አንስተው፤ ሁሉም ሰው ይህን ማወቅ እንዳለበትና ፈቃደኛ ሆኖ ወደ ሥርዓቱ በመግባት ለዚህ ስኬት መረባረብ እንዳለበት አመላክተዋል፡፡

በአሁን ወቅትም 90 ሚሊዮን ዜጎችን ለመመዝገብና ወደ ፋይዳ ወይም ወደ ዲጂታል ሥርዓት ለማስገባት ጥረት እየተደረገ መሆኑን የጠቀሱት አብዮት ባዩ (ዶ/ር)፤ ለዚህም አብዛኛው ኢትዮጵያዊ በሚኖርበት አካባቢ የኢንተርኔት አገልግሎትና የቴሌኮም መሠረተ ልማት ተደራሽ ነው፡፡ ይህም ዲጂታል መታወቂያን መጠቀም የሚያስችል ምቹ ሁኔታ መፈጠሩን የሚያመላክት ነው ብለዋል፡፡

አያይዘውም በገጠር ያለውን ማኅበረሰብ ታሳቢ በማድረግ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች በስፋት እየተሠሩ እንደሆነ ጠቁመው፤ በሚቀጥሉት ከሦስት እስከ አምስት ዓመት ባለው ጊዜ ውስጥም ከ15 ዓመት በላይ የሆነ አብዛኛው ኢትዮጵያዊ የፋይዳ ወይም የዲጂታል መታወቂያ ባለቤት ይሆናል፡፡ ይህም ኢኮኖሚያዊ ዕድገትን በማፋጠን የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ትራንስፎርም ለማድረግ ትልቅ ግብዓት ነው ብለዋል፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## ኢትዮጵያ ለአፍሪካ ኅብረት መጠናከር የተጫወተችው ሚና ዛሬም ተጠናክሮ እንደቀጠለ ነው !

ኢትዮጵያ የጥቁር ሕዝቦች የነፃነት ተምሳሌት ከመሆኗም ባሻገር የአፍሪካ ሀገራት በአንድ ጥላ ስር እንዲሰባሰቡ እና ለመብታቸው በአንድነት እንዲታገሉ ያልተቋረጠ ጥረት ስታደርግ ቆይታለች፡፡

እኤአ ግንቦት 25 ቀን 1963 የአሁኑ አፍሪካ ኅብረት የቀድሞ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ሲመሠረት ኢትዮጵያ የመሪነቱን ሚና ተጫውታለች፡፡ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት የተመሠረተባትና መቀመጫ ሆና የተመረጠችው ኢትዮጵያም ከድርጅቱ ምሥረታ ጥንስስ በሁለት እግሩ ቆሞ እስኪሄድ ድረስ የማይተካ ሚና ነበራት፡፡

ለአፍሪካ ኅብረት መመሥረት ትልቅ ሚና የነበራት ኢትዮጵያ በተለይም የካዛብላንካና የሞኖሮቪያ ቡድኖች የአፍሪካ አንድነት ምሥረታ በተመለከተ የነበራቸው ልዩነት በወይይት በማጥበብና ወደ አንድ መሥመር በማምጣት በኋላም የአፍሪካ ሀገራት አንድነትን የሚያጠናክር ድርጅት እንዲፈጠር ከፍተኛውን ሚና መጫወቷን የታሪክ ድርሳናት ያሳያሉ።

ኢትዮጵያ የአፍሪካ አንድነት እንዲቋቋም የአንበሳውን ድርሻ ከመያዟም ባሻገር ድርጅቱ ከተቋቋመ በኋላ ቢሆን በሁለት እግሩ እስኪቆም ኢትዮጵያ የዋለችው ውለታ በቀላሉ የሚዘነጋ አይደለም፡፡ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት መቀመጫ አዲስ አበባ እንዲሆን ከተወሰነ በኋላ ኢትዮጵያ ድርጅቱን ለማጠናከር የተለያዩ ድጋፎችን ስታደርግ ቆታለች፡፡ ከእነዚህም መካከል በወቅቱ ለፖሊስ ኮሌጅ ተብሎ የተሠራውን ባለብዙ ክፍል ሕንጻ በግምት 250ሺ ካሬ ሜትር ከሚሆን ቦታ ጋር ለድርጅቱ እንዲሆን በነፃ አበርክታለች፡፡ በተጨማሪም የአፍሪካ አንድነት እስኪጠናከር ድረስ የድርጅቱን የሦስት ዓመት ሥራ ማስኬጃ ወጪ በራሷ ስትሸፍን ቆይታለች፡፡

የኢትዮጵያ አስተዋፅዖ ከዚህም በዘለለ መልኩ የአፍሪካ ሀገራት ከቅኝ ግዛት እንዲላቀቁ እና እንደሀገር እንዲመሠረቱም የማይዘነጋ አስተዋፅዖ አበርክታለች፡፡ በዓለም ላይ የተለያዩ ንቅናቄዎች እንዲቀጣጠሉም ማዕከል ሆና አገልግላለች፡፡

አፍሪካውያን ገና ነፃ ባልወጡባቸው ዓመታት ኢትዮጵያ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት አባልነቷ ለነፃነታቸው ተከራክራላቸዋለች፡፡ እኤአ. በ1958 ኢትዮጵያ ለ200 አፍሪካውያን ነፃ የትምህርት ዕድል ሰጥታለች። በዚህ የትምህርት ዕድል ኬንያ፣ ታንጋኒካ፣ ዛንዚባር፣ ዩጋንዳ፣ ጋና፣ ናይጄሪያ፣ ሴራሊዮን፣ ግብፅ፣ ላይቤሪያ ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡ በደቡብ አፍሪካ ሻርፕ ቪል ሰልፍ ላይ በመጋቢት 21 ቀን 1960 በግፍ የተገደሉ ሰዎች ልጆችን ሙሉ ወጪያቸውን ችላ የአፍሪካውያንን ልጆች አስተምራለች፡፡

ኢትዮጵያ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት እንዲመሠረት ብቻ ሳይሆን አሕጉሪቱ ከቅኝ ግዛት ቀንበር እንድትላቀቅ የነፃነት ትግሉን በመደገፍ አዎንታዊ አበርክቶ የነበራት ሲሆን ለአብነትም ደቡብ አፍሪካ ከአፓርታይድ ሥርዓት እንድትላቀቅ በኋላ ላይም ለዚምባብዌ የነፃነት ትግል ስኬት ያደረገችው አስተዋፅዖ ተጠቃሽ ነው።

ኢትዮጵያ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ከተመሠረተ በኋላም ዋነኛ ዓላማዋ የነበረውን አፍሪካን ከቅኝ ግዛት የማላቀቅ ዓላማ ተግባራዊ ለማድረግ በተቋቋመው ኮሚቴ ውስጥ አስተባባሪ ከሆኑ ሀገሮች መካከል ኢትዮጵያ አንዷ ነበረች፡፡ የኮሚቴው ዋነኛ ዓላማም የአፍሪካ ሀገራት ከቅኝ አገዛዝ ቀንበር ለመላቀቅ የሚያካሂዱትን ትግል በገንዘብ መርዳት ነበር፡፡ ከዚህ በተጨማሪም አፍሪካን ከቅኝ አገዛዝ ጨርሶ ለማላቀቅ በሚደረጉ ትግሎች አንደኛው ዘርፍ የሆነውን የዲፕሎማሲ ሥራ መሥራትንም ያካትታል፡፡ ለነፃነት የሚዋጉ አፍሪካውያን ኃይላቸውን ወደ አንድ አሰባስበው እና ልዩነታቸውን ትተው ግንባር እንዲፈጥሩ ማደራደርም ሌላኛው ተልዕኮ ነበር፡፡

የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ተልዕኮውን ጨርሶ ወደ አፍሪካ ኅብረት ሲሸጋገርም ኢትዮጵያ የማይተካ ሚና ተጫውታለች፡፡ የአፍሪካ ኅብረት እንዲጠናከርም መዲናዋ ዘመናዊ መሰብሰቢያ አዳራሽ እንዲገነባ ቦታ ከመስጠት ጀምሮ በማስተባበር ተሳትፋለች፡፡ ዛሬም አዲስ አበባ ዘመናዊነት የተላበሰች ከተማ እንድትሆን ዘርፈ ብዙ ተግባራት በመከናወን ላይ መሆኑ እሙን ነው፡፡

የኅብረቱ መቀመጫ የሆነች አዲስ አበባ ዛሬ ስሟን የሚመጥኑ ሥራዎችን እየተከናወኑባት ነው፡፡ ሰፊ በሆነ የኮሪደር ልማት አውታር ዘመናዊ የተሽከርካሪ መንገዶች፣ የእግረኛ መተላለፊያዎች፣ መብራቶች፣ የደኅንነት ካሜራዎች፣ መናፈሻዎች እና መዝናኛዎችን አዲስ አበባን እንደስሟ አስውበዋታል፡፡

ቀደም ሲል በፅዳት ጉድለት እና በመሠረተ ልማት እንዲሁም በዘመናዊ ሆቴሎች እጥረት ስሟ ሰርክ የሚነሳው አዲስ አበባ ዛሬ ፅዱ እና ውብ ከተማ ሆና በ38ኛው አፍሪካ ኅብረት ጉባኤ የሚሳተፉ እንግዶቿን በጉጉት በመጠባበቅ ላይ ትገኛለች፡፡

## አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ
- አልማዝ አያሌው

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ለሰላም ሁላችንም እንትጋ!

ትንሳዔ አበራ

ሰላም የሁሉ ነገር መሠረት ነው:: ወጥቶ ለመግባት፣ ሰርቶ ለመለወጥ፣ ወልዶ ለመሳምም ሆነ ለማሳደግ፣ ዘርቶ ለማጨድ፣ ወዘተ፣ ሰላም በእጅጉ ያስፈልጋል:: ለቤተሰብም፣ ለአካባቢም፣ ለሀገር ብሎም ለመላ ዓለምም ሰላም ወሳኝ ጉዳይ ነው::

ሀብት የሚገኘው ሀገር ስትጎዳና ስትደማ ብለው የሚያስቡ በአቋራጭ መበልፀግ የሚፈልጉ አካላት ካልሆኑ በስተቀር፣ የሰላም እጦት ሊመቸው የሚችል አንድም ሰብዓዊ ፍጡር አይኖርም:: ምክንያቱም የሀገሮችም ሆነ ሕዝቦች እድገትና ብልፅግናም ከሰላም ውጪ አይታሰብም::

አንዳንዶች ይህን ላይገነዘቡት ይችላል፤ ከዚህ ይልቅ በተለምዶ የሰላም ጥቅሙ የሚታወቀው ሰላም እጦት ሲያጋጥም ነው ይላሉ:: የሰላም ጥቅሙ እንደተባለው በእዚህ ወቅት ሊታወቅ የሚችልበት ሁኔታ እንዳለ ሁሉ አርቆ ላሰበው ደግሞ የሰላም ጥቅሙ በደህናውም ቀን በእጅጉ ይታወቃል:: ይሁን እንጂ የሰላምን ዋጋ እንድንገነዘብ እየተደረገ ያለው በዓለም ከሚታዩት ጦርነቶችና ግጭቶች መካከል ሆኗል:: አዎን ከዚህ የሰላም እጦት የሚያስከፍለውን ዋጋ እያየን ነው::

በሀገሮች መካከል የሚደረጉ ጦርነቶች፣ በሀገር ውስጥ የሚደረጉ የእርስ በርስ ግጭቶች፣ የሽብር ተግባሮች ሰዎችን ለችግሮች እየዳረጉ ናቸው:: የሰው ሕይወት በከንቱ እየጠፋ፣ ሀብትና ንብረት እየወደመ ይገኛል:: እናም ሰላምን ለመጠበቅ፣ ለማምጣትና ለማስፈን የመንግሥታት፣ የሃይማኖት ተቋማት፣ በሰላም ላይ የሚሠሩ አካላት ሚና ከፍተኛ ነው፤ የእያንዳንዱን ግለሰብና ማኅበረሰብ ጥረትና ትጋት ይጠይቃል::

በዚህ ረገድ በሰላም እጦት ውስጥም ሆነው ስለ ሰላም ቀን ተሌት የሚተጉና ሰላምን አጥብቀው የሚሹ እንዳሉ ይታወቃል:: በአንጻሩ የእናት ሆድ ዥንጉርጉር እንዲሉ ቁጥራቸው ጥቂት ቢሆንም የራሳቸው የፖለቲካ ዓላማ፣ ወይም የሌሎች ፀረ ሀገርና ሰላም ኃይሎች ተላላኪነት ተጠናውቷቸው በፀረ ሰላም ድርጊት ሀገርና ሕዝብም የሚያቆስሉ መኖራቸውን እያየን ነው::

እነዚህ ሰላም ጠሎች ያሰቡትን ያሳኩ እየመሰላቸው ማወካቸውን አይተውም፤ ሀገር አማን ሆኖ የተናወጠ አርገው ያወራሉ፤ ያስወራሉ:: የመንግሥትን ሥራዎች ሁሉ በማጥላላት ሕዝብ በመንግሥት ላይ እንዲነሳ አጥብቀው ይሠራሉ:: የእርስ በርስ ግጭት እንዲኖር በማድረግ፣ የልማት ተቋማትን ሥራቸውን እንዳይሠሩ በማወክ፤ ሌሎች የልማት ተቋማት እንዳይመሠረቱ ሽብር በመንዛት፣ ወዘተ፣ ሰላምና መረጋጋት እንዳይኖር ይጥራሉ::

ኢትዮጵያ በዚህ አይነቶቹ የፀረ ሰላሞች እኩይ ድርጊቶች ብዙ ተፈትናለች:: ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እንዲሁም ፖለቲካዊ ቀውስ እንዲፈጠርም ሲደረግ ቆይቷል::

መንግሥት ልማት ላይ እንዳያተኩር፣ ግጭት በማብረድና ሰላምና መረጋጋት ላይ እንዲጠመድ በማድረግ በሀገርና ሕዝብ ላይ ብዙ እኩይ ተግባር ፈጸመዋል:: ሆኖም እነሱ እንዳሰቡት ሳይሆን መንግሥትና ሕዝብ እንዳሰቡት ሆኖ ልማቱም ተጠናክሮ ቀጥሏል፤ በአንዳንድ ክልሎች ደፍርሶ የነበረው ሰላምም ቢሆን ከእጁ አላወጣም፤ ይልቁኑም እየተጠናከረ መጥቷል::

ለዛሬ ብቻ ሳይሆን ለነገን ማሰብም የሚቻለው ሰላምና ሰላም ሲኖር ብቻ ነው:: ለዚህ ደግሞ በልዩነቶች ላይ ተቀራርቦ በመወያየት ችግሮችን በቀላሉ በመፍታት ሰላም ማውረድ ሲቻል ነው:: ምክንያቱም ይሄን ባለማድረግ የኃይል አማራጭን በመከተል በተፈጠሩ ግጭቶች ባለፉት ዓመታት በሀገራችን የተፈጠረው ጥፋት ምን ያህል ሕዝብና ሀገርን እንደጎዳ በሚገባ ይታወቃል::

ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦችን በአንድነት አቅፋ በያዘችው ኢትዮጵያ፣ በመተሳሰብና በመቻቻል እሴቶቿ ስሟ በበጎነት በሚነሳው ኢትዮጵያ፣ ይህን ማንነቷን የማይመጥን የሰላም መደፍረስ ባለፉት ዓመታት ታይቶባታል:: በሀገሪቷ የተለያዩ አካባቢዎች በተከሰተ የፀጥታ መደፍረስ የተነሳ ሀገር ተጎድታለች:: ዜጎች ተረጋግተው እንዳይሠሩ ሆነዋል::

ሀገራችንን ከሌሎች ሀገራት ለየት ከሚያደርጓት መካከል አንዱ ግጭቶችን በማስቆም የሚታወቁ የቱባ ባሕልና መልካም እሴቶች ባለቤት መሆኗ ይጠቀሳል:: ከእነዚህ እሴቶች መካከል በማኅበረሰቡ ዘንድ የተለመዱት የሽምግልናና የእርቅ ሥርዓቶች ይጠቀሳሉ:: እነዚህ እሴቶች ሰውና ሰውን ይቅርና እንስሳትን ከሰው ጋር እንደሚያስታርቁ ይነገርላቸዋል::

ለምሳሌ፣ ጋሞዎች በእዚህ የለውጥ ዘመን ሊያጋጥም የነበረን አንድ ግጭት ቀጥ አርገውበታል:: በመሆኑም የእነዚህን እሴቶች አቅም በአግባቡ መጠቀምና በየቦታው የሚታዩና የሚፈጠሩ ግጭትና የሰላም ችግሮችን እልባት እንዲያገኙ መሥራት ይገባል::

ከዚህ ባለፈ ጊዜውን (ያለንበትን 21ኛው ክፍለ ዘመን) የሚመጥን አካሄድን መከተል ይገባል፤ ችግሮች ከመፈጠራቸው በፊትም ሆነ ከተፈጠሩ በኋላ በጠረጴዛ ዙሪያ ቁጭ ብሎ መነጋገርን::

ምክንያቱም አለመግባባት ውስጥ የገቡ አካላት ሲሆን ሲሆን በራሳቸው አለያም በሦስተኛ ወገን አነሳሽነት በችግሮቻቸው ላይ በጠረጴዛ ዙሪያ በመወያየት መፍታት ይጠበቅባቸዋል:: ይሄን የሚያደርጉት ደግሞ ለሕዝብና ለሀገር ሰላም እንዲወርድ ለማድረግ ነው:: በዚህም ሀገሮችና ሌሎች የተለያዩ ወገኖችም ችግሮችን ፈተዋል::

በእኛም ሀገር ይሄን መሰል አያሌ አብነቶች ቢኖሩም፤ በአንዳንድ ቡድኖች አሻፈረኝ ባይነት ልዩነቶች ሰፍተው ግጭት ውስጥ የተገባባቸው ሁኔታዎች ጥቂት የሚባሉም አይደሉም:: ሆኖም ዛሬም አለመግባባቶችን በውይይት ለመፍታት መንግሥት ቁርጠኛ ነው:: ይህንን ቁርጠኝነቱን ሁሌም ከመግለጽ ባለፈ፤ መሣሪያ አንስተው ጫካ ከገቡ አካላት ጋር ለመወያየት በመወሰን፣ በመወያየትም ጭምር አሳይቷል:: ይህን ተከትሎም ጫካ የገቡ ታጣቂዎች ችግሮችን በውይይት ለመፍታት በመወሰን መሣሪያቸውን አስቀምጠው ተመልሰዋል::

ለምሳሌ፣ በኦሮሚያና በአማራ ክልል መሣሪያ ይዘው ሲንቀሳቀሱ የነበሩ ኃይሎች በቅርቡ ለሀገርና ለወገኖቻቸው ሰላም ሲባል የቀረበውን የሰላም ጥሪ ተቀብለው ሰላማዊ አማራጭን ብለው ወደ ተሐድሶ ሥልጠና ማዕከላት ገብተዋል:: በአፋር፣ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልልም እንዲሁ መሣሪያ ይዘው ጫካ የገቡ አካላት ወደ ሰላማዊ አማራጭ ፊታቸውን መልሰዋል::

የሰላም እጦት ለማንም የሚበጅ አለመሆኑን አውቀውና ተረድተው፣ ለሕዝብና ለሀገር ብለው አጀንዳቸውን አቅርበው በጠረጴዛ ዙሪያ ለመመከር ፈቃደኛ በመሆን ወደ ሥልጠና ማዕከላት የገቡ እነዚህ ወገኖች ዘመኑ የሚጠይቀውን የሰላም አማራጭ ተከትለዋልና ሊመሰገኑ ይገባቸዋል:: ሌሎች መሣሪያ አንስተው ጫካ የገቡ አካላትም ይህን የመንግሥትን የቆየ የሰላም መንገድ ሊጠቀሙበት እንዲሁም ሌሎች የተከተሉትን የሰላማዊ መንገድ አማራጭ መከተል ይገባቸዋል::

መንግሥትም ዘላቂ ሰላም ለማስፈን እያደረገ ካለው ጥረት ጎን ለጎን ለሰላም ትልቅ ዋጋ የሚሰጡትን መንፈሳዊና ባሕላዊ እሴቶቻችንን በመጠቀም በኩል የሰላም እናቶች፣ የሀገር ሽማግሌዎችና የሃይማኖት ተቋማት በባለቤትነት መሥራታቸውን ማጠናከር ይኖርባቸዋል:: እሴቶቻችን ሰላምን ለማጽናት፣ ግጭትን ለማስቆም ለምን አልቻሉም የሚለውን በጥናት በመለየት ሊሠራባቸው ይገባል::

ግጭትን ሳይሆን ሰላምን፣ ልዩነትን ሳይሆን አብሮነትን ስንቅ በማድረግ ለሀገራችን ሰላም እና ለሕዝቦች አንድነት መትጋት የሁሉም ዜጋ ኃላፊነት ሊሆን ይገባል::

ሰላም እንደ መና አይወርድም:: የዜጎችንና የሀገርን ሥራ ይፈልጋል:: ይህንንም ባለፉት ዓመታት በሚገባ ተመልክተናል:: በሀገራችን የተለያዩ አካባቢዎች የተከሰቱ ግጭቶች የቆሙትና ወደ ሰላማዊ ሁኔታ መመለስ የተቻለው መንግሥትና ሕዝብ በከፈሉት ዋጋ ነው::

በሀገሪቱ ሰላም እንዲሰፍን እያንዳንዱ የሚጠበቅበትን ኃላፊነት መወጣት ይኖርበታል:: የሰላም እጦት ሕዝብና ሀገርን ምን ያህል እንደሚጎዳ በሚገባ ተመልክተናል:: ይህን ሁሉ ቆም ብሎ ማሰብ ያስፈልጋል::

ከግጭትና ከጦርነት ያተረፈ ሀገርና ሕዝብ የለምና ሁሉም ሌት ከቀን ለሰላም መትጋት ይኖርበታል:: እያንዳንዳችን ለሰላም ተሚጋችና ተቆርቋሪ ልንሆን ይገባል:: ቸር እንሰንብት::

ፖለቲካ እና ወቅታዊ

## ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

# የኢትዮጵያ የአረብ ሊግ የአባልነት ጥያቄ እና ቀጣናዊ ፋይዳው

እስማኤል አረቦ

የአረብ ሀገራትን አንድነት እና የጋራ ብልፅግናን ለማረጋገጥ በሚል ዕሳቤ እኤአ በ1945 በግብጽ ካይሮ የአረብ ሊግ ተቋቋመ። የአረብ ሊግ በመካከለኛው ምስራቅ፣ በሰሜን አፍሪካ፣ በምስራቅ አፍሪካ እና ደቡብ ምስራቅ አፍሪካ ያሉ ሀገራትን በማቀፍ የተቋቋመ ሲሆን፣ በአሁኑ ወቅትም 22 ሀገራትን በቋሚ አባልነት እንዲሁም አራት ሀገራትን በታዛቢ አባልነት ይዞ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል።

ቋሚ አባል ሆነው ሊጉ ውስጥ እንቅስቃሴ እያደረጉ ያሉት 22 አባላት ግብጽ፣ ሞሮኮ፣ ጂቡቲ፣ አልጄሪያ ፣ ባህሬን፣ ኮሞሮስ፣ ኢራቅ፣ ጆርዳን፣ ኩዌት፣ ሊባኖስ፣ ሊቢያ፣ ሙርታኒያ፣ አማን፣ ፓልስቲን፣ ኳታር፣ ሳኡዲ አረቢያ፣ ሱማሊያ፣ ሱዳን፣ ሶርያ፣ የተባበሩት አረብ ኤምሬት እና የመን ናቸው። በታዛቢነት ደግሞ ብራዚል፣ ህንድ፣ ቬንዚላ እና ኤርትራ ይገኙበታል።

ሊጉ በቋሚ አባልነት ለመመዝገብ በመስፈርትነት ካስቀመጣቸው ነጥቦች ውስጥ አባል ለመሆን የሚጠይቁ ሀገራት የሥራ ቋንቋ አረብኛ መሆኑ፣ ከፍተኛ ቁጥር ያለው የሙስሊም ማህበረሰብ መኖሩ የሚሉት ይጠቀሳሉ። ሊጉ ከተመሠረተ 80 ዓመት የተጠጋው ሲሆን በእነዚህ ዓመታት የአረቡ ዓለም የተረጋጋ ሰላም እና የተፋጠነ ልማት እንዲኖረው ዓላማ አንግቦ ሲንቀሳቀስ ቆይቷል።

ሆኖም ሊጉ በዓላማነት ይዟቸው ከተነሳቸው ነጥቦች ውስጥ በልማት እና እድገት ዘርፍ የተሻለ ሥራ መሥራት ችሏል። ሊጉ ከተመሠረተ ጀምሮም አብዛኞቹ አረብ ሀገራት በእድገት የተሻለ ደረጃ ላይ መድረስ ችለዋል። ሊጉ አልተሳካለትም ተብሎ የሚታሰበው በአረብ ሀገራት የተረጋጋ ሰላምና ደህንነት ማስፈን አለመቻሉ ነው። ለዚህ ደግሞ አንዱ ምክንያት የሚባለውና ብዙዎች የሚያምኑበት በአባል ሀገራቱ መካከል ተመሳሳይ የፖለቲካ አተያይ አለመኖር ነው።

ለምሳሌ፣ ሊጉ እኤአ በ1950 የጋራ የሚሊቴሪ እና የደህንነት ተቋም እንደሚመሰርት በዕቅድ ቢያስቀምጥም እስካሁን በዚህ ረገድ የታየ ለውጥ የለም። በዚህም በሊጉ ውስጥ የሚገኙ ሀገራት አብዛኞቹ ውስጣዊ ሰላም የሌላቸው እና ሶርያ፣ የመን፣ ሊቢያ፣ ፓላስቲን የመሳሰሉ ሀገራት በማያባራ ጦርነት ውስጥ መሆናቸው እና ሊጉም ጠብ የሚል መፍትሔ ማምጣት አለመቻሉ ጥርስ የሌለው አንበሳ አስመስሎታል።

ይሄም ሆኖ ግን ከዚህ በተቃራኒ የአረብ ሊግ ሀገራት በዓለም የኢኮኖሚ እና የፖለቲካ እንቅስቃሴ ውስጥ እየተጫወቱት ያለው ሚና እያደገ መጥቷል። ግብጽ፣ የተባበሩት አረብ ኤምሬት፣ ኳታር፣ ሳኡዲ አረቢያን የመሳሰሉ ሀገራት ከኢኮኖሚ ግስጋሴያቸው ባሻገር ከመካከለኛው ምስራቅ እስከ አውሮፓ ድረስ ተደማጭነታቸው እያደገ መምጣቱ ብዙዎች የአረብ ሊግን በትኩረት እንዲያዩት እና እንዲፈልጉት አስገድዷቸዋል።

አረብ ሊግ ሀገራት በአረቦች እና በእስራኤል መካከል ለሚነሳው ግጭት እና ጦርነት በአሸማጋይነት የሚመረጥ እና የአረቡን ዓለም እና አውሮፓን አስማምቶ ለመሄድ ድልድይ ሆኖ የሚያገለግል ተቋም እየሆነ መምጣቱ ተፈላጊነቱን ጨምሮታል። ወደ ቀይ ባሕር እና በኤደን ባሕረ ሰላጤ አካባቢ ስንመጣ ደግሞ፣ የሊጉ አባል ሀገራት ወሳኝ ሚና ሲጫወቱ እንመለከታለን።

አብዛኞቹ ሊጉ አባል ሀገራት ከቀይ ባሕር እና የኤደን ባሕረ ሰላጤ ጋር የቅርብ ቁርኝት ያላቸው እና በአካባቢው ላይ ተደማጭነት ያላቸው መሆኑ እንደ ኢትዮጵያ ያሉ ሀገራትን ትኩረት መሳቡ አይቀሬ ነው። ቀይ ባሕር በሜዲትራንያን በኩልም ሆነ በህንድ ውቅያኖስ የነዳጅ ዘይት ለሚጭኑ መርከቦች ዋና የባሕር መንገድ ነው። በዚሁ ባሕር ላይ በዓመት ከ3ሺ በላይ መርከቦች የተለያዩ ዕቃዎችን ጭነው ይመላለሳሉ። በአጠቃላይም ቀይ ባሕር ካለው ስትራቴጂክ ሥፍራነት በተጨማሪ 40 በመቶ የሚሆነው የዓለም የንግድ ልውውጥ በዚሁ ባሕር ላይ እንደሚከናወን መረጃዎች ይጠቁማሉ።

በአሁኑ ወቅትም ሳኡዲ አረቢያ፣ የመን፣ ግብጽ፣ ሱዳን፣ እስራኤል፣ ዮርዳኖስ፣ ኤርትራና ጅቡቲ በጋራ የቀይ ባሕር ባለቤቶች ናቸው። ኢትዮጵያ ከዚህ መድረክ ከተገለለች ከ33 ዓመታት በላይ ተቆጠሩ። ይህ መሆኑ ደግሞ ከቀይ ባሕርና ከኤደን ባሕረ ሰላጤ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ተጠቃሚነቷ ውጭ እንድትሆን አስገድዷታል።

**በነቢዩ መሐመድ ይህን ያህል የገዘፈ ክብር ያላትን ኢትዮጵያና ዜጎቿን በፍቅር አለመቀበል ከነቢዩ ትዕዛዝ እንደ መውጣት የሚቆጠር ነው፡፡ ስለዚህም ታላቁ ነቢዩ የተቀበሏትን ሀገር የአረብ ሊግ በአባልነት አልቀበልም ለማለት የሚያስችል ሃይማኖታዊም ሆነ ታሪካዊ መሠረትም የለውም**

ኢትዮጵያ ለሺህ ዓመታት የቀይ ባህር ንጉሥ ሆና የኖረች ሀገር ነበረች። ስለዚህም ኢትዮጵያ ወደ ቀደመ ማንነቷ ወደ ቀይ ባሕር መመለስ አለባት። ለዚህም በአሁኑ ወቅት የባሕር በር አማራጮችን በሰላማዊ መንገድ በማፈላለግ ላይ ትገኛለች። ይህ ሰላማዊ ጥያቄ አፋጣኝ መልስ እንዲያገኝ ከእነዚህ ሀገራት ጋር በቅርበት መሥራት ያስፈልጋል። ለዚህ ደግሞ አረብ ሊግ አባል ከመሆን የተሻለ አማራጭ የለም።

ዋነኛዋ አረብ ሊግ አባል ግብጽ ደግሞ ዘወትር ከኢትዮጵያ ጥቅም በተጻራሪ የምትቆም በመሆኑ፣ የግብጽን ሴራ ለማክሸፍ ኢትዮጵያ ሊጉን መቀላቀል ይኖርባታል። ይህንኑ መነሻ በማድረግም ኢትዮጵያ የአረብ ሊግ የአባልነት ጥያቄ አቅርባለች። ጥያቄውም ከበርካታ እይታዎች አንጻር ተገቢነት ያለው ነው።

በመጀመሪያ የአረብ ሊግ ያስቀመጣቸውን መስፈርቶች በሙሉ ታሟላለች። ኢትዮጵያ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ሙስሊም ማህበረሰብ የሚኖርባት ሀገር ነች። በሊጉ ውስጥ ያሉ አስር ሀገራት ውስጥ የሚኖረው የሙስሊም ሕዝብ ቁጥር በኢትዮጵያ ካለው ሙስሊም ሕዝብ ቁጥር ያነሰ ነው። ይህም ኢትዮጵያ የተሻለ ተቀባይነት እንዲኖራት ያስችላል።

በሁለተኛነት፣ በኢትዮጵያ ውስጥ ከፍተኛ ቁጥር ያለው አረብኛ ተናጋሪ ሕዝብ አለ። በአፋር፣ ሶማሌ፣ በቤኒሻንጉል ጉሙዝና በሌሎችም አካባቢዎች በርካታ ሕዝብ አረብኛ ቋንቋን ይናገራል። ከዚህም ባሻገር የስልጤ ዞን እና የቤኒሻንጉል ክልል አረብኛ በትምህርት ሥርዓቱ ውስጥ ተካቶ የሚሰጥ ቋንቋ ሆኗል።

ከእነዚህ ሁሉ ወቅታዊ ሁኔታዎች ባሻገር ደግሞ ኢትዮጵያ ለእስልምና ሃይማኖት መስፋፋት ብሎም ለሙስሊሙ ማህበረሰብ ያበረከተችው አስተዋጽኦ በታሪክ የሚዘነጋ አይደለም። ኢትዮጵያ ከመካ ቀጥሎ እስልምናን የተቀበለች የመጀመሪያዋ ሀገር እና ሙስሊም ስደተኞችን ተቀብላ በፍቅር እና በርህራሄ ያስተናገደች ባለውለታ ሀገር ነች።

ኢትዮጵያ ስደተኞችን የመቀበል ታሪኳ የሚጀመረው ከመካ ተሰደው የመጡ የእስልምና እምነት ተከታዮችን ተቀብላ ከማስተናገዷ ጋር በተያያዘ ነው። ነብዩ መሐመድ የእስልምና እምነትን ለማስፋፋት ሲነሱ በመካ የነበሩ የባዕድ እምነት ተከታዮች ተቃወሟቸው። ተቃውሟቸውም እስከ ማሳደድና የአማኞችንም ሕይወት እስከ ማጥፋት የደረሰ ነበር።

በዚህ የጭንቅ ወቅት ነቢዩ መሐመድ ተከታዮቻቸውን ለሁለት ጊዜ ያህል ወደ ኢትዮጵያ በመላክ ከባዕድ አማኞቹ ጨካኝ በትር ማዳን ችለዋል። ይህን ዓለም አቀፋዊ መልዕክት መሠረት ለመጣል በወቅቱ እንደ ሀገር፣ እንደ መንግሥትና እንደ ሕዝብ መስዋዕትነት የከፈለ ከሀበሻ በቀር ማንም የለም።

ሀበሻ እንደ ሀገር፣ አስሃማ እንደ ንጉሥ፣ ሀበሾች እንደ ዜጋ በነቢዩ ሙሐመድ (ሰዐወ) በኩል በጊዜው የተሰጣቸው ክብር ምን እንደሚመስል ከነቢዩ (ሰዐወ) ሀዲሶች፣ ከሙስሊም ደራሲያን የተዘገቡትን በመጠኑም ቢሆን እናስቀምጣለን። አላህ (ሱወ) ምሁራንና ከሚጠቁማቸው እንጂ ከራሳቸው የማይናገሩት ነቢዩ ሙሐመድ (ሰዐወ) ሐበሻን፣-

**1ኛ፡- «የእውነት ምድር» ብለዋታል**፣ ይህ አባባል ምንም እንኳ መካ የተከበረው የአላህ ቤት የሚገኝበት ቢሆንም በወቅቱ ፍትህና እውነት ስለጠፋ ነቢዩ ሙሐመድ (ሰዐወ) እና ተከታዮቻቸው ለስቃይና ለችግር ተጋልጠው ነበር። የሚፈለገው ፍትህና እውነት ግን በሐበሻ መሬት በጊዜው ተግባራዊ መሆን ችሏል። ስለዚህ ነቢዩ ሙሐመድ (ሰዐወ) ሲታገሉለት የነበረው ፍትህና እውነት ከመካ ከ16 ዓመት በፊት በሀበሻ ምድር እውን ሆኖ ነበር። ለዚህ ነው ሀበሻ የፍትህና የእውነት ምድር በመሆን መካን የቀደመችው።

**2ኛ፡- የማይበድል ሀቀኛ ንጉሥ ያለባት ሀገር** ትባላለች። ይህም በዘመኑ በአካባቢው የተለያዩ ነገሥታት ቢኖሩም፣ ሀቀኛና ፍትሀዊ ንጉሥ የነበረው ግን ነጃሺ ብቻ ነበር።

**3ኛ፡-«እሱ ዘንድ ማንም በደል አይደርስበትም»** የተባለውም ሀገሪቷ የእውነት ምድር በመሆኗ፣ ንጉሡም ፍትሀዊ በመሆኑ፣ እሱ ዘንድ ማንም ሰው ቀለም፣ ቋንቋ፣ ብሔር ሳይገድበው ሰብዓዊ መብቱና ክብሩ ይጠበቅለትና ይከበርለት ስለነበር ነው።

ለዚህም ነው ስደተኞች ምንም እንኳ ከሀበሻ ጋር ቋንቋ፣ ብሔር፣ ባሕል፣ ወግ፣ ቀለም ባያዛምዳቸውም፣ ባደረጉት የ16 ዓመት ቆይታ በእነሱ ላይ የተፈፀመባቸው ግፍም ሆነ በደል ፈፅሞ አልነበረም። እምነታቸውን በነፃነት ተግባራዊ እያደረጉ ከመንግሥትም ሆነ ከሕዝቡ አስፈላጊ ድጋፍ፣ ድጎማና እንክብካቤ እየተደረገላቸው መቆየት ችለዋል። የስደት ቆይታቸውን ጨርሰው እስከሚመለሱ ድረስ ከነሱ ውስጥ አንድም ቅሬታ ያቀረበ ስደተኛ አልነበረም። እንዲያውም ለሀበሻ ምድር፣ ለንጉሡና ለሕዝቧ ከፍተኛ ፍቅርና ክብር ነበራቸው።

**4ኛ፡- በዘመኑ በመንግሥት ደረጃ እስልምናን በማስተናገድ ሀበሻ የመጀመሪያ የመንግሥት ሀገር ነች**። እስልምናን በመቀበልም ከመካ ቀጥላ ሁለተኛ ነች። በግለሰብ ደረጃም ቢሆን በወንዶች ሀበሻ ሁለተኛ ነች። ይህም ቢላል ቢን ረባህ አል ሐበሺ (ረዓ) እስልምናን በመቀበል ከአቡበከር (ረዓ) ቀጥሎ ሁለተኛው አማኝ በመሆኑ ነው።

ኢብነል አቲር የሚባሉት ዘጋቢ እንደጠቀሱት ነቢዩ ሙሐመድ (ሰዐወ) ኡካዝ በሚባል የገበያ ማዕከል ለተሰበሰበው ሕዝብ ኢስላማዊ ጥሪ ያስተላልፉ ነበር። አንድ አምር ቢን አበሳህ የሚባል ታዋቂ ግለሰብ ነቢዩን (ሰዐወ) እንዲህ ሲል ጠየቃቸው። «ይህን ጥሪህን ማን ተቀበለህ?» አላቸው «አቡበከርና ቢላል» ብለው መለሱለት።

ከሴቶች ኢትዮጵያዊቷ ኡሙ አይመን (ረዐ) ከኸድጃ (ረዐ) ቀጥላ ነው እስልምናን የተቀበለችው። በሀገር ከመካ ቀጥላ ሀበሻ ነች። በአህጉር አንደኛ አፍሪካ ነች። የእውነት ምድር በመባል ከመካ በ16 ዓመት እንቀድማለን። የእስልምና መመሪያን በተለይ ዘካና ፆምን በመቀበልና በመፈፀም ከመካ በ6 ዓመት ሀበሻ ትቀድማለች። በጂሀድ በመሰዋዕት የመጀመሪያው መሀጃ አልሐበሺ (ረዐ) ነው። ኢስላማዊ ስደትን ዓለም አቀፋዊና በማስተናገድ ሀበሻ የመጀመሪያዋ ሀገር ነች።

ሀበሻ እንደ ሀገር፣ ንጉሥ አስሃማ እንደ ንጉሥ፣ ሀበሾች እንደ ዜጋ ነበሩ ለነቢዩ (ሰዐወ)፣ ለተከታዮቻቸውና ለመልዕክቱ በቅድሚያ አዎንታዊ መልስ ሰጥተዋል። ይህን በማድረጋቸው በቁርዓንም ሆነ በነቢዩ (ሰዐወ) ሀዲስ በልዩ ሁኔታ ለሀበሾች ለየት ያለ ክብር ተሰጥቷቸዋል። እሳቸውም (ሰዐወ) በልዩ አቋማቸው ለሀበሾች ልዩ ከበሬታ ሰጥተዋል። ከእነዚህ ከበሬታዎች መካከልም፡-

1ኛ፡- ሀበሻን በተመለከተ «ሀበሾች እስካልነኳችሁ ድረስ አትንኳቸው» የሚል ነቢያዊ መመሪያ ሰጥተዋል። ይህም ቃላቸው በሱነን ኢብን ዳውድ ተመዝግቦ ይገኛል። ተከታዮቻቸውም ይህንን ተግባራዊ በማድረግ እስልምናን ለማሰራጨት በምስራቅ እስከ ቻይና፣ በምዕራብ እስከ ፈረንሳይና ስፔይን፣ ወደ ሰሜንና ምዕራብ አፍሪካ ድረስ ዘመቻ ሲያካሂዱ ወደ ሐበሻ ምድር የተደረገ አንድም ዘመቻ አልነበረም።

ይህንን ነቢያዊ ትዕዛዝ ተግባራዊ ከማድረግ አንፃር ሀበሻ በነቢዩ (ሰዐወ) ጊዜ የተደረገውን ስደተኞችን መቀበል ብቻ ሳይሆን ከዚያም በኋላ በተለያዩ ጊዜያት በተከሰቱ የፖለቲካ አለመግባባትም ሆነ የኢኮኖሚ ችግር የአካባቢው ነዋሪዎች ወይም በውጊያ የተሸነፉ ሁሉ እየመጡ ተጠልለውባታል። ይኸውም በሙዓዊያዎች፣ በአባሲዮች፣ በዑስማኒዮች ዘመናት ተሸናፊ ሁሉ ወደ ሀበሻ እየተሰደዱ የመጡ ሲሆን፣ ሀበሻ ለሁሉም መጠለያና መጠጊያ ስትሆን ቆይታለች።

**2ኛ፡- ነቢዩ ሙሐመድ (ሰዐወ) በ8ኛው ዓመተ ሂጅራ** በእስልምና ታሪክ ውስጥ ትልቅ ክብርና ታሪክ የፈፀሙት መካን በመክፈት መሆኑ ይታወቃል። ይህም ከ21 ዓመት ትግል በኋላ ቁረይሾችን ድል በማድረግ ነበር መካን የከፈቱት። በዚያ ዕለት ፍትህና ሀቅ በመካ ስለተረጋገጠ «የእውነት ምድር» የሚለው ነቢያዊ አባባል ተግባራዊ መሆን ቻለ። አላህም (ሱወ) በቁርዓን ሱረት ኢስራ ምዕራፍ አንቀፅ 81 ላይ «እውነት ተረጋገጠ፣ ስህተት ተደመሰሰ» ሲል ያበሰረበት ዕለት ነበር።

በዚያን ዕለት የተቀደሰው የአላህ ቤት ካዕባ ከጣዖታት አምልኮ ነፃ ሆኖ ለባለቤቱ ለአላህ (ሱወ) ተመለሰ። በዚያም ከ360 ያላነሱ ጣዖታት ሲደመሰሱ የነቢዩላህ ኢብራሂም (ዐሰ) ጸሎት መልስ ያገኘበት፣ በሰማይ ያለው የአላህ ቤት በምድር ካለው ጋር ግንኙነት ያደረገበት፣ በሰማይ የሚገኙ መላዕክታት ሁሉ ሱጁድ በመውረድ ለጌታቸው ምስጋና ያቀረቡበት ዕለት ነበር።

በዕለቱም ነቢዩ ሙሐመድ (ሰዐወ) ሐበሾችን በተመለከተ ሁለት ልዩ ከበሬታ ሰጥተዋል። አንደኛው፣ በካዕባው ውስጥ የነበሩት ጣዖታትን ሙሉ በሙሉ ለማስወገድ ስለፈለጉ ዑስማን ኢብን ጦልሃ (ረዓ) የሚባለውን የካዕባውን ቁልፍ ያዥ የተቀደሰውን ካዕባ እንዲከፍት አዘዙት፣ እሱም ትዕዛዙን በማክበር ከፈተላቸው። የካዕባው በር እንደተከፈተ ሁሉም _ የነቢዩ (ሰዐወ) ተከታዮች በተለይ የቅርብ ጓደኞቻቸው የሆኑት እነ አቡበከር (ረዓ)፣ ዑመር (ረዓ)፣ ዑስማን (ረዓ)፣ ዓሊ (ረዓ) እና ሌሎቹም ከነቢዩ (ሰዐወ) ጋር ወደ ካዕባው ውስጥ አብረው ለመግባት በጉጉት ይጠብቁ ነበር።

ነቢዩ (ሰዐወ) ግን አብረዋቸው እንዲገቡ የመረጡት በጣም የሚወዱትና የሚያከብሩት የአሳዳጊያቸው ልጅ የሆነውና መካን ድል ባደረጉበት በዚያ ዕለት ካዕባን ሰባት ጊዜ ጡዋፍ ሲያደርጉ ግመላቸው ላይ አብሮ ተቀምጦ አብሯቸው ካዕባን ሰባት ጊዜ ጡዋፍ ያደረገው የሀበሻይቱ እመቤት የኡሙ አይመን (ረዓ) ልጅ ዑሳማ ቢን ዘይድ (ረዓ) እና ልዩ ቃል አቀባያቸውና ሙአዚናቸው ቢላል ቢን ረባህ አል ሐበሺ (ረዓ) ብቻ ነበሩ። ሁለቱ ሀበሾች ከሌሎች በልጠው በነቢዩ ተመራጭ ነበሩ። ኢብኑ ዑመር በዘገቡት ሀዲስ ነቢዩ (ሰዐወ) «ሀበሻን በቤቱ ያስገባ ትሩፋት ያገኛል» ብለዋል።

ስለዚህም በነቢዩ መሐመድ ይህን ያህል የገዘፈ ክብር ያላትን ኢትዮጵያና ዜጎቿን በፍቅር አለመቀበል ከነቢዩ ትዕዛዝ እንደ መውጣት የሚቆጠር ነው። ስለዚህም ታላቁ ነቢዩ የተቀበሏትን ሀገር የአረብ ሊግ በአባልነት አልቀበልም ለማለት የሚያስችል ሃይማኖታዊም ሆነ ታሪካዊ መሠረትም የለውም።

**ማስታወሻ፡- ይህንን ጽሑፍ ሳዘጋጅ በዋነኝነት በረዳት ፕሮፌሰር አደም ካሚል የተጻፈውን €€ሀበሾች በነቢዩ ዙሪያ« እንዲሁም €€ረጅሙ የኢትዮጵያ የዲፕሎማሲ ጉዞ«፤ McGuf›n, S. (2017). Moving Toward Regional Integration of the Arab League. Old Dominion University የተሰኙትን መጻሕፍት በማጣቀሻነት ተጠቅሚያለሁ።**

ኢኮኖሚ

# ሳይንስና ቴክኖሎጂ

## ለጀማሪ ቢዝነስ ባለሙያዎች ምቹ ምህዳር የፈጠረው ፕሮጀክት

**ወርቅነሽ ደምሰው**

ባለፈው ዓመት የኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ከኮሪያ ዓለም አቀፍ ትብብር ኮይኮ /KOICA/ ጋር በመተባበር አይሲቲ ፓርክ ውስጥ "ኢኖቢዝ-ኬ ኢትዮጵያ" "Innobiz-K Ethiopia Center" የተሰኘ የኢኖቬሽን ማዕከል መገንባቱ ይታወቃል:: ማዕከሉ ፈጠራን በማጎልበት፣ ጀማሪ ስታርታአፖችን በማብቃት እና የኢኮኖሚ እድገትን በማፋጠን ረገድ ትልቅ ምዕራፍ ይከፍታል ተብሎ የተመነበት ነው::

ማዕከሉ በኢንፎርሜሽን፣ ኮሙኒኬሽንና ቴክኖሎጂ (በአይሲቲ) ዘርፍ የቢዝነስ ሃሳብ ያላቸውን ስታርትአፖች ለማበረታታት እና ለመደገፍ በቅድሚያ ስታርትአፖችን እያወዳደረ ያሰለጥናል::

ዘንድሮም ፕሮጀክቶችን በመቅረጽ ጀማሪ የቢዝነስ ባለሙያዎችን /ስታርትአፖች/ን እያወዳደረ ድጋፍ ማድረጉን ቀጥሏል:: በዚህም ላለፉት አምስት ወራት 24 ስታርትአፖች የፋይናንስ፣ የገንዘብ አስተዳደር፣ የገበያ ልማትና መሰል ሥልጠናዎችን እንዲያገኙ አደርጓል።

የድህረ ስታርትአፕ ፕሮጀክት ላወጣው ውድድር 55 ስታርትአፖች የተመዘገቡ ሲሆን፣ ወደ ፕሮጀክቱ ለመግባት ብቃት አላቸው ተብለው የታሰቡት ግን 24 ስታርትአፖች ናቸው:: እነዚህ ስታርትአፖች በሦስት ዙሮች የተከፋፈሉ ሥልጠናዎች እንዲያገኙ ተደርጓል::

በመጀመሪያ ዙር 24ቱም ለሦስት ቀናት የቆየ ሥልጠና እንዲያገኙ የተደረገ ሲሆን፤ ከመካከላቸው 12ቱን በመመረጥ ደግሞ ለሌላ የአምስት ወራት ተከታታይነት ያለው ሥልጠና ተሰጥቷቸዋል:: በእነዚህ አምስት ወራት በስምንት አማካሪዎች( አራት የሀገር ውስጥና አራት የኮሪያ) ድጋፍ ሲደረግላቸው መቆየቱ ተጠቁሟል::

ከሥልጠናው በኋላ 12ቱ የቢዝነስ ስትራቴጂ፣ የፋይናንስ አያያዝና አስተዳደር፣ የገበያ ልማትና ሽያጭ ስትራቴጂ፣ የድርጅት አስተዳደር እውቀታቸው እንዲጎለብትና በሌሎች የተሻለ እውቀትና ግንዛቤ እንዲያገኙ መደረጉ ከአፈጻጸማቸው መታየቱም ተመላክቷል::

ባለፈው ሳምንት መጨረሻም የእነዚህ ስታርትአፖች እውቅናና ሽልማት መርሃ ግብር ተካሂዶ፣ 12 ስታርትአፖች የላቀ ውጤት በማስመዝገባቸው እውቅናና ሽልማት ተበርክቶላቸዋል። ከእነዚህ መካከል ሁለት ስታርትአፖች ተመርጠው ለቀጣዩ ፕሮግራም እንዲያልፉና ሌላ የሁለት ወራት ተከታታይ ስልጠናና ድጋፍ እንዲያገኙ እንደሚደረግ ተገልጿል::

በእውቅና ሽልማት መርሃ ግብር ላይ የኮሪያ ዓለም አቀፍ ትብብር ‹‹ኮይካ› አስተባባሪና የጀማሪ ቢዝነሶች ባለሙያ ቾይ ዮንግ (ዶ/ር) ባደረጉት ንግግር እንደተናገሩት፤ ድህረ ስታርትአፕ ፕሮጀክት ጀማሪ ቢዝነሶችን በማበረታታት ትልቅ እድገት እንዲያስመዘግቡ እያደረገ ነው::

የድህረ ስታርትአፕ ፕሮግራሙ ለሶስት ዙር የተካሄደ ሲሆን፣ የመጀመሪያው አጠቃላይ ፕሮግራም ሁሉም ስታርትአፖች ሥልጠና እንዲያገኙ የተደረገበት ነው:: ሁለተኛው ደግሞ ወደ ሁለተኛ ዙር ላለፉ ስታርትአፖች ላለፉት አምስት ወራት የተሰጠው ሥልጠና ሲሆን፣ ሦስተኛው ኢንቪስት እንዲያደርጉ ድጋፍ የተደረገበት ነው::

ኮይኮ ላለፉት ዓመታት ለ24 ስታርትአፖች ድጋፍ መስጠቱን አስታውሰው፤ ዘንድሮም 12 ስታርትአፖች የፋይናንስ፣ የብራንድ፣ የገንዘብ አስተዳደር፣ የገበያ ልማትና መሰል ሥልጠናዎችን እንዲያገኙ ማድረጉን ይገልጻሉ::

የእነዚህ ስታርትአፖች የላቀ ውጤት ማስመዝገብ ለኢትዮጵያ ቀጣይ እድገት አስተዋጽኦ እንዳለው አመልክተው፣ ሀገራቸው ለኢትዮጵያ በዘርፉ የምታደርገውን ድጋፍ አጠናክራ እንደምትቀጥል አረጋግጠዋል::

በመርሃ ግብሩ ላይ የተገኙት የኢኖቪሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስትር ዴኤታ ባይሳ በዳዳ (ዶ/ር) እንዳስታወቁት፤ ፕሮጀክቱ እውቀትን ለማጎልበት፤ ምርትና ምርታማነትንና ፈጠራን ለማሳደግ አስተዋጽኦ እያበረከተ ይገኛል:: የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ዘርፍ በተለይ ስታርትአፕ በሰው ሀብት ብዛት ከአፍሪካ ሁለተኛ ለሆነችውና ኢትዮጵያ ትልቅ ዕድል ነው::



ፕሮጀክቱ በኢትዮጵያ ኢኮኖሚው በእውቀት እየተገነባ መሆኑን እንደሚያመላክትም ጠቅሰው፤ ሂደቱም ፈጠራና ፍጥነትን ማዕከል እያደረገ እንዲሆን እያደረገ መሆኑንም ይገልጻሉ:: ተልዕኮችን በዋናነት በእውቀት ላይ የተመሠረተ በፈጠራ የሚመራ ኢኮኖሚ መገንባት ነው ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፣ ይህን ፍጥነቱን በመጨመር ብልፅግና እውን የሚሆንበትን ጊዜ ለማሳጠር እንደሚያስችል ጠቁመዋል::

እሳቸው እንደሚሉት፤ ዘርፉ በራሱ ሥራና ሀብት እንዲሁም ለሌሎች ዘርፎች አስቻይ ሁኔታን ይፈጥራል:: በዚህም ምርትና ምርታማነት በእጅጉ እንዲያድግ አስተዋጽኦ ያበረክታል:: በግብርና፣ በጤና፣ በትምህርት፣ በማህበራዊ እና በመሳሰሉት ዘርፎች ላይ የሚያበረክተው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው:: በግብርና ብክነትን በእጅጉ በመቀነስ እንዲሁም ምርታማነት እንዲጨምር በማድረግ አስተዋጽኦ ያበረክታል::

በኢንዱስትሪ ዘርፍም እንዲሁ ከምርምር ተቋም የሚወጣ እውቀትን፣ ከሌላ ሀገር የሚፈጠር የእውቀት ሽግግርን ተጨባጭ በማድረግ ተኪ ምርቶች በሀገር ውስጥ በስፋት እንዲመረቱ ያስችላል:: እነዚህን ምርቶች ለውጭ ገበያ ለማቅረብ ይረዳል::

ከምርምር ተቋማት ጋር በሠራናቸው ሥራዎች ከውጭ የሚገቡ ግብዓቶች በሀገር ውስጥ እንዲመረቱ ማድረግ እየቻልን ነው ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ ባለፉት ጥቂት ዓመታት ብቻ ጥቂት የማይባሉ ከውጭ የሚመጡ ምርቶችን በሀገር ውስጥ መተካት ተችሏል ሲሉም ተናግረዋል::

ይህም ዘርፉ እጅግ በጣም አስፈላጊና ከትንሽ ተጀምረው የሚያድጉ ፈጠራ የታከለባቸው /ኢኖቪቲቭ/ ኢንዱስትሪዎች እንዲኖሩ እንደሚያስችል ጠቁመዋል:: የሰው ሀብት ጥራትን ለማሳደግ እንደሚጠቅም፣ የሥራ ክህሎት፣ እውቀትና የመረዳት አቅምን በመደመር ወደ ፈጠራ በመቀየር አዳዲስ ፕሮጀክቶችና አገልግሎቶች መፍጠር እንዲቻል እንደሚያደርግ ጠቁመዋል:: ዘርፉ ለዚህ ከፍተኛ ሚና እየተጫወተ እንደሚገኝም ያመላክታሉ::

እሳቸው እንዳስታወቁት፤ የአገልግሎት ኢንዱስትሪውን ለማዘመንም ይጠቅማል:: የሀገሪቱ የአገልግሎት ኢንዱስትሪ እንዲሁም የመንግሥት አገልግሎት በኢኮሜርስ ወይም ሌሎች ንግዶች ለማቀላጠፍ አስተዋጽኦ ሊያበረክት ይችላል:: የአገልግሎት ኢንዱስትሪው በሁሉም ረገድ ቀልጣፋ ፈጣንና ዘመናዊ እንዲሆን ለማድረግም ይጠቅማል:: ተወዳዳሪ ተቋማት እንዲኖሩ ያደርጋል::

ባለፉት አምስት ዓመታት ምርምርን መነሻ ያደረጉ ተቋማት መፈጠር ጀምረዋል ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ ሌሎች ሀገራትና እንደ አፕል፣ ሳምሰንግና የመሳሰሉት ኩባንያዎች በየጊዜው ምርቶቻቸውን እያሻሻሉ ተፎካካሪ እንደሆኑ ሁሉ፤ ሀገር ውስጥ ያሉ ተቋማትም ሥራቸውን በምርምር በማገዝ ምርቶቻቸውን ለሀገር ውስጥ ግብዓት ብቻ ሳይሆን ለውጭ መላክ እንዲችሉ ለማድረግ ጥረት እየተደረገ መሆኑንም ጠቅሰዋል::

ለዚህ ውጤታማነት መንግሥት ለዘርፉ የሰጠው ትኩረት ከፍተኛ ሚና መጫወቱን አስታውቀዋል::

**ፕሮጀክቱ እውቀትን ለማጎልበት፤ ምርትና ምርታማነትንና ፈጠራን ለማሳደግ አስተዋጽኦ እያበረከተ ይገኛል:: የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ዘርፍ በተለይ ስታርትአፕ በሰው ሀብት ብዛት ከአፍሪካ ሁለተኛ ለሆነችው ኢትዮጵያ ትልቅ ዕድል ነው**

ከለውጡ ማግስት ጀምሮ ችግሮችን በፖሊሲ ለይቶ ድጋፍ ሲያደርግ መቆየቱን ጠቅሰው፤ የቴሌኮም አገልግሎት ለውድድር ክፍት መደረጉን ለዚህም በአብነት ጠቅሰዋል:: ሌላ ኦፕሬተር ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገባ በር ከመክፈቱም በተጨማሪ ኢትዮ ቴሌኮምም የራሱን አቅም አውጥቶ በተሻለ መልኩ መሥራት እንዲችል ማድረጉን ገልጸዋል:: በዚህም ድርጅቱ አቅሙን በማውጣት ባከናወነው ተግባር ሀገራዊ አቅም ማሳደግ መቻሉንም ተናግረዋል::

ባለፉት ጥቂት ዓመታት ከመሠረተ ልማት አንጻር ለስታርትአፕ ምቹ ምህዳር መፈጠሩን ጠቅሰው፣ ከ60 በላይ የኢንኩቤሽን ማዕከላት እንዲገነቡ መደረጋቸውን ገልጸዋል:: ማዕከላቱ የመንግሥት፣ የግል፣ በግልና በመንግሥት በጋራ ተገንበተው እየሠሩ መሆኑን አመላክተዋል::

እሳቸው እንደሚሉት፤ የምርምር ተቋማት እውቀት እያመነጩ ናቸው:: ሲባክን የኖረውን ተሰጥኦ ወደ ሀብት የመቀየር ሥራ እየተሠራ ይገኛል:: እነዚህ ተሰጥኦ ያላቸው ወጣቶች ለሀገራቸው መሥራት እንዲችሉ ተስማሚ ምህዳር መገንባት አስፈላጊ ስለሆነ ከተቋም ግንባታና ከአሠራር ዘርጋታ አንጻር የተሠሩ ሥራዎችም አሉ:: የምርምር ተቋማት የራሳቸውን ተልዕኮ መሠረት በማድረግ ለዘርፉ ተሰጥኦ (ታለንት) ልማት እየሠሩ ይገኛሉ:: የተለየ ሃሳብ ያላቸው ባለተሰጥኦዎች ያለምንም እድሜ ገደብ እንዲሳተፉ የማድረግ ሥራ ተጀምሯል::

‹‹ከሰው ኃይል ልማት ብዙ ሲሠራ ቆይቷል:: በተሰጥኦ፣ በክህሎት፣ ሃሳብ ወደ ምርት እንዲቀይር፤ ወደ አገልግሎት እንዲቀየር የማድረግ ሥራ እየተሠራ ይገኛል:: ይህንንም ከመሠረቱ ከመደገፍ አንጻር የአምስት ሚሊዮን ኮደር ኢኒሼቲቭ ሥልጠና ተግባራዊ እየተደረገ ይገኛል:: ከሀገሪቱ ሕዝብ 70 በመቶ የሆነው ወጣት በዚህ ሥልጠና በመሳተፍ በቂና አስፈላጊ እውቀት እንዲያገኝ ለማድረግ መንግሥት በከፍተኛ ትኩረት እየሠራ ነው›› ብለዋል::

የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ለዘርፉ ምቹ ምህዳር ለመፍጠር፣ ችግሮች ካሉም ችግሮቹን በማጥናት እየፈታ ከዓለም ሁኔታዎች ጋር ለመራመድ እንደሚሠራ ጠቅሰው፤ ከሀገር ውስጥና ዓለም አቀፍ ተቋማት ጋር በመተባባር ለዘርፉ ድጋፎችን እንደሚያደርግም አመላክተዋል::

ሚኒስቴር ዴኤታው እንዳብራሩት፤ ባለፉት ጥቂት ዓመታት ምህዳሩ በከፍተኛ ሁኔታ አድጓል:: ይህም ለዘርፉ ሥራ ምቹ ሁኔታ መፍጠር ችሏል:: ምህዳሩ በእጅጉ እያደገ የመጣው መንግሥት ለዘርፉ በሰጠው ትኩረት ነው:: የመንግሥት እንዲሁም የልማት አጋሮችና የሀገር ውስጥ ተቋማት ትስስርና ቅንጅት እየጨመረ መጥቷል:: በመንግሥት በኩል ከሀገር ውስጥ አካላት ጋር ብቻ ሳይሆን በውጭ ከሚገኙ ተቋማት ጋርም በትብብር ለመሥራት ጽኑ ፍላጎት አለ::

የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ለስታርትአፕ ምቹ ምህዳር ከመፍጠርና ምህዳሩን ከማስፋት አንጻር ብዙ ሠርቷል፤ ይህን ተከተሎም ለውጦች መጥተዋል፤ ውጤቶች እየተመዘገቡ ናቸው:: ለዚህም ባለፉት አምስት ወራት ብቻ በተደረገው ድጋፍ የተገኘውን ውጤት ማየት ይቻላል::

ዘርፉ ሀገርንም መቀየር የሚችል ነው:: በትንሽ አቅም ብዙ ሥራዎች መሥራት ያስችላል:: ይህንን ዘርፍ በደንብ ማየትና መገንዘብ ያስፈልጋል::

ወጣቶች የአምስት ሚሊዮን ኮደርስ ኢኒሸቲቭ ሥልጠናን በመከታተል ክህሎታቸውን ማሳደግ አለባቸው:: ከዚያም ችግሮችን በመረዳትና መፍትሔ የሚያመላክቱ የፈጠራ ሃሳቦችን ማመንጨት ይጠበቅባቸዋል:: ይህንን ማድረግ የሚያስችል ምቹ ሁኔታና ምህዳር ተፈጥሯል፤ ይፈጠራልም:: ለዚህም መንግሥት ድጋፍ ያደርጋል፤ ወጣቶች ይህንን ተገንዝበው በዘርፉ መሰማራት አለባቸው::

"ዘርፉ ለብዙዎች የሥራ እድል ይፈጥራል፤ አንድ ኩባንያ ብዙ ኩባንያዎችን መፍጠር የሚችልበትም ነው:: አንድ ቦታ የሚቀር ብቻ አይደለም፤ በፍጥነት ዓለም መድረስ የሚችልም ነው:: በዚህ ዘርፍ የሚሰማራ ኩባንያ ለራሱ ብቻ ሳይሆን ለዓለም ብርሃን መሆን የሚችል መሆን አለበት::

በኢትዮጵያ በአጭር ጊዜ ኢኮኖሚያዊ እድገትን ለማምጣትና ዘላቂና ተሻጋሪ ልማት እውን ለማድረግ ዘርፉ ወሳኝ ሚና እንዳለው አስታውቀው፤ ከራስ በማለፍም ለአፍሪካና ለሌሎች የዓለም ሀገራት መትረፍ ያስችላል ብለዋል::

በመጨረሻም ከ12ቱ ስታርትአፖች ከገቢ አንጻር ስታይ 150ሺ ብር ተነስቶ በእጥፍ አድጎ እድገቱን ወደ አምስት እጥፍ ማሳደግ የቻለው አብዲ ኤሌክትሮ መካኒክስ የተሰኘ ስታርትአፕ እንዲሁም በ150 ሺ ብር ተነስቶ 80 በመቶ ያህል እድገት ያሳየው መድኃኒት የተሰኘ ስታርታአፕ ተመርጠው የ10 ሺህ ዶላር የማበረታቻ ሽልማት ተበርክቶላቸዋል::

# ወቅታዊ ትንታኔ

# የኢኮኖሚ ሪፎርሙ ትሩፋቶችና ቀሪ የቤት ሥራዎች

**አስቴር ኤልያስ**

የተሟላ የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ቁልፍ ዓላማዎች ተብለው ከተጠቀሱት መካከል አንዱ የገንዘብ ፖሊሲ ማሕቀፍን በማዘመንና የመንግሥትን ፋይናንስ አስተማማኝነትን በማረጋገጥ የዋጋ ንረትን መቀነስና መቆጣጠር ተጠቃሽ ነው:: የውጭ ምንዛሪ መዛባትን ማስተካከልና የረጅም ጊዜ የውጭ ክፍያ ሚዛን ጉድለት ችግሮችን መፍታት ደግሞ ሌላኛው ነው:: የመንግሥትን እዳ አስተማማኝነት ማረጋገጥና የመንግሥትን የኢንቨስትመንትና ቅድሚያ ትኩረት የሚሰጣቸውን የወጪ ፍላጎቶችን ለመሸፈን የሀገር ውስጥ የገቢ አሰባሰብን ማጠናከርም እንዲሁ ከዓላማው ዝርዝር ውስጥ የሚካተት ነው::

ኢትዮጵያ ወደዚህ የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ የመግባቷ ምስጢር የተመሰቀቃቀለውን የማክሮ ኢኮኖሚ ሚዛን ለመጠበቅ እንደሆነ ይነገራል:: ይህንንም በማስተካከል ኢትዮጵያ ያለባትን የእዳ ጫና ለመቀነስ የሚያስችል ሲሆን፣ በተለይም ምርትና ምርታማነትን ይበልጥ ለማሳደግም በመፈለጉ ነው:: ከዚሁ ጋር ተያይዞ ዜጎች በሥራ አጥነት ችግር ውስጥ እንዳይገቡም ሲባል በኢኮኖሚው ውስጥ ያሉትን ማነቆዎች መፍታት አስፈላጊ በመሆኑ ነው::

ከዚሁ ከማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ጋር ተያይዞ የፕላንና ልማት ሚኒስትር ፍጹም አሰፋ (ዶ/ር) ሰሞኑን ማብራሪያ መስጠታቸው ይታወቃል:: እርሳቸው እንደሚሉት፤ ትልቁ የኢትዮጵያ የረጅም ጊዜ የኢኮኖሚ ልማት፤ አጠቃላይ የልማት ጉዞ ማነቆ የነበሩት የኢኮኖሚ ፖሊሲዎቻችን የተገበርናቸው ፖሊሲዎች ካላሳኩልን ነገሮች ውስጥ አንዱ መዋቅራዊ ሽግግር መምጣት አለመቻሉ ነው::

ከዚህ በፊት የነበሩት የሀገራችን የኢኮኖሚ ፖሊሲዎች ኢኮኖሚውን በፈለግነው ደረጃ ሊያሻግሩልን አልቻሉም የሚሉት ሚኒስትሯ፣ ለዜጎችም የሚሆን የጋራ ብልፅግና ማረጋገጥም ተስኗቸው ቆይቷል ሲሉ ያስረዳሉ:: ለዚህ አለመሳካት ምክንያት የሆነው ደግሞ የሀገሪቱ የሥርዓታት ጉድለት መሆኑንም አስታውሰው፤ እነዚህ መዋቅራዊ ጉድለቶቻችን በፖሊሲዎች፣ በሕጎችና በአሠራር የሚገለጹ በርካታ ችግሮች የነበሩባቸው ናቸው ብለዋል::

እንደእርሳቸው ገለጻ፤ ከዚህ አኳያ ከአስር ዓመቱ እቅድ ጋር አብሮ ለአስር ዓመቱ ትግበራ አስቻይ ሁኔታ የሚፈጥር የመጀመሪያው ምዕራፍ የሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ ተግባራዊ ተደርጓል:: በዚህ የሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ ምዕራፍ የመዋቅራዊ ጉዳዮች በጣም ትልቅ ቦታ ተሰጥቷቸዋል:: እነዚህም ኢኮኖሚያችንን የበለጠ ዘመናዊና ለውድድር ክፍት ማድረግን የያዙ ናቸው::

ከዚህ በፊት 50 እና 60 ዓመታት ያስቆጠሩ ሕጎች ነበሩን፤ የንግድ ሕጋችንን ጨምሮ ከዚያም መለስ ያሉ አዋጆች በርካታ ነበሩ:: ከዚህ ውስጥ የኢንቨስትመንት አዋጅ አንዱ ነው:: በመሆኑም በመጀመሪያ ምዕራፍ ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ ላይ ወደ 80 የሚጠጉ ሕጎች ተቀይረዋል:: ከዚያ በተጨማሪ በርካታ አሠራሮች ተከልሰዋል፤ አገልግሎት የሚሰጥባቸውም መንገዶች የአንድ መስኮት አገልግሎት እንዲሆኑ ተደርገዋል:: የንግድና ኢንቨስትመንት ከባቢ የተሻለ ለማድረግም የተሠሩ ሥራዎች አሉ::

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ገዥ አቶ ማሞ ምህረቱ በጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት ፕሬስ ሴክሬታሪያት ኃላፊ ከሆኑት ከቢልለኔ ስዩም ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ እንደተናገሩት፤ በሀገር በቀሉ የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ወደ ሥራ የተገባው ዋና እና ወሳኝ የሆኑ ቁልፍ ጉዳዮችን በመለየት ነው:: እነዚህም ሴክተሮች ቁልፍ ጉዳዮች ግብርና፣ አይ.ሲ.ቲ፣ ቱሪዝም፣ ማዕድን እና ማኑፋክቸሪንግ ናቸው:: ከዚህም የተነሳ የተደረገው ማሻሻያ አግባብነት ያለው መስመር ተከትሎ እየተጓዘ ነው::

ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያው ሶስት መሠረታዊ ነገሮችን የያዘ ነው ያሉት አቶ ማሞ፣ የመጀመሪያው የማክሮ ኢኮኖሚ ፕሮግራም ይፋ በተደረገበት ወቅት በዓለም አቀፍ ማኅበረሰብ ጭምር ድጋፍ ነበር ብለዋል:: በተለይም ሪፎርሙ በዓለም ባንክና በዓለም አቀፉ የገንዘብ ድርጅት ድጋፍ ይደረግ እንደነበር ተናግረዋል:: ማሻሻያው በዚህ መልኩ ከዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ በርካታ ፍላጎት እንደነበር አስታውሰው፤ ከዚህ የተነሳ ጅማሬው በጣም ጥሩ የሚባል እንደሆነ ገልጸዋል::

ይሁንና ይላሉ አቶ ማሞ፣ ጅማሬው ምንም እንኳ ጥሩ የነበረ ቢሆንም እኤአ በ2020 ኮቪድ፣ በ2022 ደግሞ በኢትዮጵያ በሰሜኑ የሀገሪቱ ክፍል ጦርነት መከሰቱን ያስታውሳሉ:: ቀጥሎም የዩክሬኑ ጦርነት እንደተከሰተና እነዚህ ሁሉ ተግዳሮቶች በኢኮኖሚው ላይ ያሳደሩት ጫና ቀላል የሚባል እንዳልሆነ ያመለክታሉ:: እንዲያም ሆኖ ግን ይላሉ ዋና ገዥው፣ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ በእነዚህ ሁሉ ተግዳሮቶች ውስጥ ቢያልፍም ሳይበገር ውጤት ማስመስዝገብ መቻሉን ተናግረዋል::

እርሳቸው እንደሚሉት፤ ኢትዮጵያ ያለፈው ሐምሌ ወር ተግባራዊ ያደረገችው የሀገር በቀል የኢኮኖሚ ሪፎርም ሁለተኛ ምዕራፍ ሰፊ እና ብዙ ዘርፎችን የያዘ ነው:: ይህ የማክሮ ኢኮኖሚ ሪፎርም ለኢኮኖሚው መረጋጋት እና ዕድገት ከፍተኛ ሚና የሚጫወት ነው::

አቶ ማሞ፣ በሪፎርሙ ተነሳሽነት በአሁኑ ወቅት በሀገሪቱ ያለው የውጭ ምንዛሪ ፍሰት አስደናቂ መሻሻል ማስመዝገቡን ተናግረዋል:: የማዕከላዊ ባንክና የባንክ ሴክተር ክምችት በእጥፍ መጨመሩንም አስረድተዋል:: ከዚህም የተነሳ ለግሉ ሴክተር የውጭ ምንዛሪ ተደራሽነት ጨምሯል ብለዋል::

ልክ እንደ ብሔራዊ ባንክ ገዡው አቶ ማሞ ሁሉ፤ የፕላንና ልማት ሚኒስትሯ ፍጹም (ዶ/ር) ሪፎርሙ የውጭ ምንዛሪ አስተዳደራችን በገበያ እንዲመራ በመደረጉ ምክንያት ገበያ ላይ ያለው የውጭ ምንዛሬ መጠን ልውውጡ በጣም የተሻለ እንዲሆን አድርጓል ብለዋል:: የውጭ ምንዛሬ ግብይትና አጠቃላይ ግዥና ሽያጩ ከፍተኛ ለውጥ ታይቶበታል:: አጠቃላይ የውጭ ምንዛሪ ክምችቱም በ200 በመቶ መጨመሩን አስረድተዋል::

እንደ እርሳቸው ገለጻ፤ በመጀመሪያው ምዕራፍ በተደረጉ ሪፎርሞች የተገኙ ውጤቶች አሉ:: በፊስካል በኩል ማክሮ ኢኮኖሚው ላይ የመንግሥት ገቢን ከማሳደግ፤ የመንግሥትን የወጪ አስተዳደርን ውጤታማ ከማድረግ አኳያ፣ ፕሮጀክቶች ውጤታማና አዋጭ ሲሆኑ ብቻ ወደ ተግባር እንዲገቡ ከማድረግ አኳያ ብዙ ለውጥ ማምጣት ተችሏል:: በተጨማሪም የሚደረገው ድጎማ ውጤታማ የሆነ ድጎማ መሆን እንዲችልና ለሁሉም ሳይሆን ወደታለመለት ድጎማ እንዲመጣ የተደረጉ ሥራዎች መኖራቸውን ያስረዳሉ::

ከእዳ አስተዳደር አኳያም ሪፎርሙ አንድ ያደረገው ነገር ቢኖር ምንም ተጨማሪ ብድር እንዳንበደር፣ ያለንን እየከፈልን እንድናቃልል፤ ከዚያ በተጨማሪ ግን በዓለም አቀፍ ደረጃ በሚኖሩ ድርድሮች የእዳ ሽግሽግ እንድናገኝ ሲሆን፣ በዚህ መልኩ የተሠራው ሥራ በከፍተኛ ሁኔታ ውጤት አምጥቷል ብለዋል::

ከዚህም የተነሳ የእዳ ጫና መጠን መቀነስ ችሏል ያሉት ፍጹም (ዶ/ር)፣ አሁን የኢትዮጵያ የውጭ እዳ ከሀገራዊ ጥቅል ምርት አኳያ 13 ነጥብ ሰባት መሆኑን ተናግረዋል:: በቅርቡም በሁለተኛው ምዕራፍ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ፕሮግራም የተሟላ የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያን ጨምሮ በውጭ ምንዛሪ አስተዳደርና በአጠቃላይ በውጭ ምንዛሪ ገበያ ላይ ትልቅ ለውጥ ያመጣ ሥራ መሠራቱንም አብራርተዋል::

የብሔራዊ ባንክ ገዥው በበኩላቸው፤ የውጭ ምንዛሪ ሥርዓቱ ከመንግሥት ቁጥጥር ወጥቶ ወደ ገበያ መር ሥርዓት መግባቱን ይናገራሉ:: በመሆኑም የውጭ ምንዛሪ ፍሰት መጨመሩንና የባንኮችን የውጭ ምንዛሪ ክምችትን ማደግ መቻሉን እና ከዚህም የተነሳ በመደበኛ እና በጥቁር ገበያ መካከል ያለውን ልዩነት ከሰባት በመቶ በታች ዝቅ በማድረግ የጥቁር ገበያውን አቅም ማዳከም መቻሉን ያስረዳሉ።

ይህ ሪፎርም ሲደረግ ለአጭር ጊዜ ቆንጠጥ የሚያደርግ ሕመም ሊኖረው እንደሚችል የሚናገሩት ደግሞ ፍጹም (ዶ/ር) ናቸው:: ሚኒስትሯ ይህም በየቤቱ ሊገባ የሚችል ፈተና መሆኑን አልሸሸጉም:: ይህም ፈተና ከዋጋ ንረት ጋር የተያያዘ ሲሆን፣ በአንዳንድ ሸቀጦች ላይ ለውጥ ሊኖር እንደሚችል ጠቅሰው፤ ይህንን ደግሞ መንግሥት ዝም ብሎ አላለፈም ብለዋል::

> “
>
> **የውጭ ምንዛሪ ፍሰት መጨመሩንና የባንኮች የውጭ ምንዛሪ ክምችት ማደግ መቻሉን እና ከዚህም የተነሳ በመደበኛ እና በጥቁር ገበያ መካከል ያለውን ልዩነት ከሰባት በመቶ በታች ዝቅ በማድረግ የጥቁር ገበያውን አቅም ማዳከም መቻሉን ያስረዳሉ**

በመሆኑም ሪፎርሙ ሀገር በቀል ነው የተባለበት አንዱ እና ወሳኝ የሆነው አመላካች ነገር ሪፎርሙን ሲደረግ የሚጎዱ ዜጎች በመኖራቸው መንግሥት ቸል አለማለቱ የሚታወቅ ነው ብለዋል:: እንዲያውም መንግሥት የሄደው ርቀት ቢኖር የተሻለ ድጎማ መስጠት አለብኝ ወደሚል ነው:: በዚህም ምክንያት ወደ 400 ቢሊዮን የሚጠጋ ብር በዓመቱ ለድጎማው በበጀት ተመድቧል ሲሉም ተናግረዋል::

እርሳቸው እንደሚሉት፤ በዚህ ውስጥ የማዳበሪያ ድጎማ በዓመት 87 ቢሊዮን ብር የሚሰጥ ነው:: ምክንያቱም ማዳበሪያ የሚመጣው በዶላር እንደመሆኑ ማዳበሪያው ሲመጣ ውድ ይሆናል:: አርሶ አደሩ ያንን ማዳበሪያ ገዝቶ የሚጠቀምበት አቅሙ ያነሰ ስለሚሆን በዚያው መጠን ምርትና ምርታማነት እንዳይጎዳ፣ ገበያ ውስጥ የሚገባ ምርት እንዳይቀንስና ተጠቃሚው ዘንድም ተግዳሮት እንዳይፈጥር በማሰብ ድጎማው ይደረጋል::

በሌላ በኩል ደግሞ ድጎማው ዝቅተኛ ተከፋይ የሆኑ የመንግሥት ሠራተኞችን ታሳቢ ያደረገ ነው:: በተለይ ለዝቅተኛው ተከፋይ እስከ 300 በመቶ ጭማሪ ያደረገ የደመወዝ ሥራ ተሠርቷል:: ለዚሁ የደመወዝ ጭማሪ የወጣው ገንዘብ ወደ 90 ቢሊዮን ብር የሚሆን ሲሆን፣ ለአጠቃላይ የመንግሥት ሠራተኞች እንደ ድጎማ ሊቆጠር የሚችል ነው ብለዋል:: ሌላው ከዚህ በፊትም ሲደረግ የነበረና መንግሥት በትልቁ ድጎማ እያደረገ ያለው የነዳጅ ድጎማን የሚመለከት ሲሆን፣ ለዚህም 100 ቢሊዮን ብር ለነዳጅ ድጎማ በጀት በመያዝ ነዳጅንም በዚያው መጠን የሚደጎም እንደሆነ ሚኒስትሯ ተናግረዋል::

ልክ እንደ ሚኒስትሯ ፍጹም(ዶ/ር) ሁሉ የብሔራዊ ባንክ ገዥው አቶ ማሞ በበኩላቸው፤ በማሻሻያው ዜጎች እንዳይጎዱ የደመወዝ ጭማሪ እና በመሠረታዊ ፍጆታ ዕቃዎች ድጎማዎችን ማድረግ ጨምሮ ምርታማነትን ለማሳደግ የተለያዩ ሥራዎች መከናወናቸውን አስረድተዋል:: ማሻሻያው ዝቅተኛ ገቢ ባላቸው የኅብረተሰብ ክፍሎች ላይ የሚያመጣውን ጫና ለመቋቋም መንግሥት የበጀት ድጎማ አሠራር የደመወዝ ጭማሪ ማድረጉን አስታውሰዋል:: የደመወዙ ብቻ ሳይሆን እርሳቸውም እንደ ሚኒስትሯ ሁሉ የነዳጅ፣ የማዳበሪያ እና መሰል ድጎማ መደረጉንና እየተደረገ መሆኑን አመልክተዋል::

አመራሮቹ እንደሚሉት ከሆነ፤ ሪፎርሙ፣ ምርታማነትን ከፍ በማድረግ ረገድ ሚናው የጎላ ነው:: በተለይም ደግሞ ዜጎች ሥራ እንዲያገኙ በማድረጉ ረገድ የሚጫወተው ሚና ትልቅ ነው:: በአሁኑ ወቅትም ይህንኑ እና ሌሎች መሰል ተግባራትን ውጤታማ ለማድረግ እየተሠራ ይገኛል:: በዚህም ተከታታይ የሆነ የኢኮኖሚ እድገት ለማስመዝገብ የሚሠራ ይሆናል::

በአጠቃላይ መዋቅራዊ የሆኑ የሕግና የፖሊሲ ማሻሻያዎች ሲጤኑ በርካታ ለውጦችን አምጥተዋል:: ይሁንና ሪፎርም ሲደረግ በጣም መልካም ነገር ብቻ አለው ማለት እንዳልሆነ ልብ ሊባል ይገባል፤ ምንም ዓይነት ተግዳሮት አያመጣም የሚል እይታም እንደሌለው መረዳቱ ተገቢ ነው::

የኢኮኖሚ ሪፎርሙ ተግባራዊ ከተደረገበት ያለፉት ስድስት ወራት ያለው አፈጻጸም እንደሚያሳየውም ኤክስፖርቱም በከፍተኛ ሁኔታ ጨምሯል:: ዘንድሮ በስድስት ወር ብቻ የተመዘገበው የኤክስፖርት ውጤት አምና በዓመት ውስጥ ከተመዘገበው ጋር ሲነጻጸር ተቀራራቢ ነው:: በወርቅም በቡናም የመጣው ከፍተኛ ለውጥ ሲታይ በጣም ከፍተኛ እምርታ ያሳየ ነው:: ይህም በኢኮኖሚው ውስጥ የነበረውን መዛባት የሚባለውን የዋጋ አለመስተካከልን በማስተካከል የመጣ ለውጥ ነው:: ይህ ውጤት መምጣት የተቻለውም ኮንትሮባንድ በከፍተኛ ሁኔታ በመቀነሱ ነው:: ይህ የሆነው በሪፎርሙ በተወሰዱ ርምጃዎች አማካይነት ነው::

በሌላ በኩል ሪፎርሙ የንግድና የኢንቨስትመንት አካባቢን የተሻለ ማድረግ ያስቻለ ነው:: የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንትም በጣም ከፍተኛ ተግዳሮትን ያስቀረ ሪፎርም ነው:: ከዚህ በፊት ኢንቨስተሮች ኢትዮጵያ ውስጥ ትልቁ ችግር አድርገው የሚያነሱት ፈተና ከውጭ ምንዛሪ ጋር ተያይዞ ያለውን የአስተዳደር ጉዳይን ነው:: ከዚህ አኳያ ከፍተኛ እምርታ ማስመዝገብ በመቻሉም ከፍተኛ ለውጥ እየመጣ ይገኛል::

ማህበራዊ

# ሴቶች

# ጥቃቱን ለመግታት መትጋት

ሰላማዊት ውቤ

«የዩኒቨርሲቲ ተማሪዋ በፍቅረኛዋ በጩቤ ተወግታ ተገደለች። የዚህን ያህል ዓመት ህጻን በቅርብ ቤተሰብ፣ በጎረቤት ተደፈረች፣ ሙሽራዋ በአሰቃቂ ሁኔታ ግድያ ተፈጸመባት» ሌላም ሌላም:: ለጆሮ የማይጥሙ፣ ለስብእናችን የማይመጥኑ ዜናዎች ማድመጥ ከጀመርን ሰነባበትን። አሁን አሁን ምን መጣብን እስኪባል ድረስ በሴቶች ላይ የሚፈፀም ጾታዊ ጥቃት እየተባበሰ ሄዷል። ግን ለምን ? ይህን ቆም ብሎ መፈተሽ ያስፈልጋል። የወንጀለኛ መቅጫ ሕጉን መመርመር፣ ውሳኔ ሰጪዎች ጋር ያለውንም ሁኔታ መከታተል፣ የችግሮችን ምንጭ መልሰን መላለሰን መመርመር ያለብን ይመስላል። ምክንያቱም ሃይማኖተኛ በሚባል ሀገርና ሕዝብ ውስጥ ይሄ ይሆናል ብሎ ማሰብ ስለሚከብድ።

ዛሬ ላይ መልኩን ቀያየሮ ዘዴውን አርቅቆ የሚታየው የጭካኔ ጥግ በሴቶች ላይ እየተፈጸመ መሆኑን መስማት እንድንለምደውና አንድ ሁለት እያልን የምንቀበለው ተግባር እንዲሆን የምንፈቅደው እየሆነ የመጣ ይመስላል።

«በሴቶች ላይ ጥቃት መጨመሩን መስማቱ አንዳች የሚፈይደው ስለሌለ ጥቃቱን ማስቆም ላይ ትኩረት ማድረጉ ለውጥ ያመጣል ብዬ አስባለሁ» ይላል ወጣት ስንታየሁ ቤተማርያም::

አሁን ላይ የተለያዩ ማህበራት፤ የሃይማኖት አባቶች፤ የተለያዩ አደረጃጀቶች፤ የኪነጥበብ ሰዎችና ሌሎች የሕብረተሰብ ክፍሎች በዚሁ ሥራ መጠመዳቸውንም ያነሳል:: እሱ እና ጓደኞቹ የኪነ ጥበብ ሙያቸውን ተጠቅመው ባገኙት መድረክ በሕብረተሰቡ ውስጥ ግንዛቤ በመፍጠር ጥቃቱን ለማስቆም እየተጉ መሆኑን ይጠቅሳል::

ግንዛቤ ለመፍጠር በተዘጋጀው መድረክ ላይ “ያኔ ነው የማውቃት” የሚል ግጥም ማቅረቡን በማሳያነት ያነሳል:: ወጣቱ በግጥሙ በሴት ልጅ ጥቃት የሚያደርሰው ከራሷ አብራክ የወጣ፤ ከማህበረሰቡ የተቀዳ ስለመሆኑና ድርጊቱ የዘጠኝ ወር ቤቱ ከመሆኗ አንፃር ‹‹ወርቅ ላበደረ ጠጠር›› መሆኑን አንፀባርቋል:: ግጥሙ ጥቃቱን ለማስቆም የወንድ አጋርነት እና ተቀናጅቶ ተከታታይነት ያለው ሥራ መሥራት አስፈላጊ ስለመሆኑ ይናገራል::

ጥቃት የማስቆም ትግሉ በየዓመቱ የ16 ቀን ‹‹ዘመቻ የጸረ- ፆታዊ ጥቃት ቀን›› ሆኖ መቅረት እንደሌለበትም ይመክራል:: በእሱ ዕምነት ጾታዊ ጥቃትን ለማስቆም የሚደረግ ትግል ቀጣይነት ያለው ሊሆን ይገባል።

መሪጌታ ዘሪሁን አጌና ጾታዊ ጥቃትን ለማስቆም ከሚሠሩ የሕብረተሰብ ክፍሎች አንዱ ናቸው:: በሚያገለግሉበት ቤተክርስቲያን ሕብረተሰቡን ከሚያስተምሩት ትምህርት ባሻገር ተግባሩን ለማስቆም ሌት ከቀን እየሠሩ ይገኛሉ:: በቅርቡም 50 ወጣቶችን አሰባስበው ጾታዊ ጥቃት ማስቆም የሚያስችላቸው ሃይማኖታዊ አስተምህሮ የተላበሰ ሥልጠናም ሰጥተዋል:: በ‹‹ሴቶች ይችላሉ›› ማህበር እና በሌሎች መድረኮች፤ በእድሮች፤ በቡና ጠጡ መርሐ ግብሮች ላይ እየተገኙም ግንዛቤን ይፈጥራሉ::

«የሃይማኖት አባቶች በማህበረሰቡ ተቀባይነት አለን» የሚሉት መሪጌታ አስተምህሯቸው ቅዱስ መጽሐፍን መሠረት ያደረገ በመሆኑ በርግጠኝነት ጥቃቱን ማስቆም እንደሚያስችል ይናገራሉ:: በሴቶች ላይ ጥቃት ስለሚፈጽሙ ሰዎች ቅዱስ መጽሐፍን ዋቢ አድርገውም «ክፉ ሰዎችን ለክፉ ነገር አሳልፎ ሰጣቸው» ስለማለቱ ያነሳሉ:: ሴት ላይ ጉዳት እንዲያደርሱ ኃጢአትን እንዲፈጽሙ ለእግዚአብሔር እንዳይገዙ ለሀገርም የተመቸ መልካም ሥራ እንዳይሠሩ ለማይረባ አእምሮ የሰጣቸው ስለመሆኑ ያስረዳሉ:: በሴት ልጅ ላይ ጥቃት የሚፈጽሙ ሁሉ ከዚህ ድርጊታቸው እንዲታቀቡ ይገስፃሉ::

ሌላው ዑስታዝ መሐመድ ዝይን እንደ መሪጌታ ሁሉ ባገኙት አጋጣሚ በተለይም በዕምነት አስተምህሮ እና ማህበራዊ መድረኮች ላይ ለማህበረሰቡ ግንዛቤ በማስጨበጥ ጥቃቱን ለማስቆም እየተጉ ያሉ አባት ናቸው:: ቅዱስ ቁርዓንን ዋቢ አድርገው እንደሚናገሩት ጥቃት የደረሰባቸውን ሴቶች ጉዳይ ከትንሳኤ ጋር አገናኝቶ እንደሚያነሳው ይናገራሉ:: ፈጣሪ ራሳቸው ጥቃት የደረሰባቸው ሴቶች በክብር ተቀስቅሰው ፊቱ በመቆም ትክክለኛውን እውነታ እንዲናገሩ ያደርጋል:: ተገዳ ስትደፈር የደረሰባትን መከራና ስቃይ፤ ለሞት ያበቃትን ሁሉ በዝርዝር ታስረዳለች::

ያኔ እንደነዚህ ያሉ ብዙ ልጃገረዶችን ያለ ፍላጎታቸው ሲደፍሩ፤ ከዚህ ሁሉ በኋላም የቤት ልጅ እና ድንግልናዋን ጠብቃ የኖረች እንጂ ድንግልና የሌላት ሴት አላገባም፤ እያሉ ሲዘብቱ የኖሩ ወንዶች የሞት ሞት የሞቱ፤ ሰው ከሚባለው ስብዕና የወጡ ስለሆኑ ለጥያቄ እንኳን አይበቁም:: ዑስታዝ መሐመድ እንደሚሉት ታዲያ የሃይማኖት አባቶች ይሄን እውነታ ከቅዱስ ቁርዓን በመጥቀስ ጥቃት የመፈፀም ልምምድ ያላቸውን የሕብረተሰብ ክፍሎች ጭምር ማስተማር ይገባል::

እነዚህ በሴቶች ላይ ጥቃት ፈጻሚዎች ከጥፋታቸው መመለስ የሚኖርባቸው ከሞት በኋላ ሳይሆን ዛሬ መሆኑን የግድ መገንዘብ አለባቸው:: ሴት ለባሏ ብቻ ሳይሆን ለሁሉም ክብርና ዘውድ መሆኗን ማወቅ ይገባቸዋል:: ‹‹ነቢዩ መሐመድ ፈጣሪ ሁለት ሴት ልጆች ሰጥቶት እነሱን ተንከባክቦ ለአቅመ ሄዋን አድርሶ ለትዳር ያበቃ ለመጽደቅና ጀነት ለመግባት ሌላ ተግባር ሳያስፈልገው መከላከያ ይሆኑታል›› እስከሚለው ድረስ የሚዘልቅ ነው::

ዑስታዝ በምሳሌ አስደግፈው እንደሚያስረዱት፤ በእስልምናው ዕምነት ሲነገር እንደተሰማው ‹‹አንዱ ሙስሊም ነቢዩ መሐመድን ከፈጣሪዬ ቀጥዬ ልንከባከበው የሚገባኝ ማነው ይላቸዋል:: እናትህን ሲሉ ይመልሱለታል፤ ለሁለተኛ ጊዜም ቀጥሎ ሲጠይቃቸውም እናትህን ይሉታል ለሦስተኛ ጊዜ ቀጥሎ ሲጠይቃቸውም እናትህን ይሉታል:: አባትህን ያሉት ለአራተኛ ጊዜ ጠይቋቸው ነው›› ይላሉ ዑስታዝ ከሰው ልጆች መካከል ሴት የተሰጣትን ከፍተኛ ክብር ሲያብራሩ ::

እንደሳቸው ለሴት ይሄ ደረጃ የተሰጠው ዝም ብሎ ከመሬት በመነሳት አይደለም:: ዘጠኝ ወሩን በእርግዝና፤ ቀጥሎ ያለውን ጊዜያት ደግሞ ጡቷን በማጥባት፤ የቀረውን ደግሞ ከዚህች ዓለም ኑሮ ጋር በማለማመድ ያሳለፈችውን ስቃይና መከራ ታሳቢ በማድረግ ነው:: አባት ምንም ለልጁ መልካም ቢሆን ይሄን የእናትን ያህል መስዋዕትነት አይከፍልምና ከዚህ በመነሳት ማህበረሰቡ ለሴት ልጅ ክብር መስጠት ይገባዋል::

ጥቃቱን በዓመት አንዴ ሳይሆን በየሰዓቱ፤ በየሰከንዱ፤ በየአካባቢው አሳዶ ማጥፋት እንደሚገባም ይናገራሉ:: በዚህ መልኩ ማጥፋት ካልተቻለ እና በዚህ ከቀጠለ ኢትዮጵያዊያኖች ሰው ፊት ሰው ሆነን የምንቆምበት አጋጣሚ ላይኖር ይችላል ሲሉም ስጋታቸውን ይገልፃሉ:: እንደ ሃይማኖት መሪ እና አስተማሪ ሆኖ ብቻ ሳይሆን እንደተራ ግለሰብ ተግባሩን ሳያሰልሱ ማውገዝ እንደሚገባም ይመክራሉ::

በሴቶች ላይ የሚደርሰውን ጥቃት ለማስቆም በሳምንት ወይም በተወሰነ ቀን የሚዘጋጁ የሃይማኖት አስተምህሮ መርሐ ግብሮች በቂ አይደሉም የሚሉት ደግሞ ፓስተር ኢያሱ አስናቀ ናቸው:: እንደሳቸው ከመደበኛው የእምነቱ አስተምሮ ውጭ በየመድረኩ እየተገኙ ለማህበረሰቡ ግንዛቤ በማስጨበጥ ጥቃቱን ለማስቆም ሳያሰልሱ እየሠሩ ይገኛሉ:: በሴቶች የሚደርሰውን ጥቃት ለማስቆም ቀጣይነት ያለውና ቅንጅታዊ ሥራ መሥራት ተገቢ በመሆኑ ጉዳይ ያምናሉ::

እሳቸውም ቅዱስ መጽሐፍን ዋቢ አድርገው እንደሚናገሩት ቅዱስ መጽሐፍ በሴቶች ላይ የሚፈጸም ጥቃትን በእግዚአብሔር ላይ እንደሚደረግ አመጽ ነው የሚመለከተው:: ከዚህ ተነስተውም በሴቶች ላይ ጥቃት የሚፈጽሙ ሰዎች በእግዚአብሔር ላይ አመጽ ያደረጉ ስለመሆናቸው ያስረዳሉ:: የዚህ አመጽ መነሻም ኃጢአት ስለመሆኑ ይናገራሉ:: ኃጢአት መሥራት ፈጣሪን መበደል ስለመሆኑም ቅዱስ ዳዊት ብዙ ጥፋቶች ከሠራ በኋላ በፀፀት ‹‹አንተን ብቻ በድያለሁ›› በማለት መናገሩን ማሳያ ያደርጋሉ:: እኛ የሃይማኖት አባቶች በሴቶች ላይ ጥቃት ለሚፈጽሙ ሰዎች አስቀድመን እግዚአብሔርን መበደላቸውን ልናሳያቸው ይገባል›› ይላሉ::

‹‹ለሴቶች ከሴቶች በላይ የሚቆም አምላክ በሰማይ አለ›› የሚሉት እኚሁ የሃይማኖት አባት መዝሙረኛው ዳዊት በመዝሙር 68 ላይ ስለ እግዚአብሔር ዳኝነት ሲናገር የመበለቶች( የሴቶች) ዳኛ ነው ስለማለቱም ያነሳሉ:: ለእነሱ ሊሟገትላቸው የሚቆም በዘለዓለም ውስጥ እውነተኛ ፈራጅ፣ አጥፊዎችንም ደግሞ አንድ ቀን ወደ ፍፃሜ ፍርድ እንደሚያመጣቸው ዳዊት መናገሩን ይጠቅሳሉ:: በየሄዱበት ቦታ ጥቃትን ለማስቆም ሲያስተምሩም ይሄንኑ ከጥፋት የመመለስ ኃይል ያለው ቃል እንደሚጠቀሙም ያብራራሉ::

ወደ መገናኛ ብዙሃን ከወጡት፤ ለፖሊስ ሪፖርት ከተደረጉት እና ከታወቁት ውጭ በምድራችን ላይ ብዙ በደሎችን የሚለማመዱ ሰዎች አሉና እነዚህኑ እያስተማሩ መመለስ ይገባልም ባይ ናቸው:: ጥቃት ለደረሰባቸውና ፍትህ ላጡ ሴቶችም በሰማይ አንድ ተከላካይ እንዳላቸው አሳውቃለሁ ይላሉ:: ይሄም በተለይ ጥቃት የደረሰባቸው ሴቶች ለጊዜውም ቢሆን ከደረሰባቸው የሥነ ልቦና ጫና እንዲወጡና ፈጣሪያቸውን ተስፋ አድርገው እንዲኖሩ የሚያስችል ስለመሆኑ ያስረዳሉ::

ሁሉም በዚህ መልኩ በቅንጅት ቢረባረብ በሴቶች ላይ የሚደርሰውን ጫና መቀነስ፤ ጥቃቱንም ማስቆም ይቻላል:: እሳቸው ‹‹ሴቶች ይችላሉ ማህበር›› እና የተለያዩ አካላት በሚያዘጋጁት መድረክ እንዲሁም ባገኙት አጋጣሚ ተጠቅመው ጥቃቱን ለማስቆም የሚሠሩትም ይሄንኑ ታሳቢ አድርገው ነው::

ከተመሠረተ 10ኛ ዓመቱን የያዘው ሴቶች ይችላሉ ማህበር በየጊዜው በሚያዘጋጃቸው መድረኮች እንደነዚህ ያሉ የሃይማኖት አባቶችን በመጋበዝ ከሚሠሩ ማህበራት አንዱ ነው:: የማህበሩ መሥራችና ሥራ አስኪያጅ ወይዘሮ የምወድሽ በቀለ እንደሚናገሩት ማህበሩ ጥቃትን ለማስቆም በተለያየ መንገዶች በቅንጅት እየሠራ ይገኛል:: የሃይማኖት አባቶች፤ ፖሊስ፤ ተማሪዎች፤ የቤት እመቤቶች፤ ወጣቶች፤ የቡና ጠጡ እና የተለያዩ ማህበራት እና የሕብረተሰብ ክፍሎች አብረዋቸው ከሚሠሩት ውስጥ ይጠቀሳሉ::

ማህበሩ አሁን ላይ አባል የሆነበት የኢትዮጵያ ሴቶች ማህበራት ቅንጅት ኔትወርክም ሆነ ሌሎች አካላት ጥቃቱን ለማስቆም እንደ አማራጭ ይዘው በዋነኛነት እየሠሩበት ያለው ይሄው የቅንጅትና ተከታታይነት ያለው አሠራር መሆኑንም ይናገራሉ::

እሳቸው እንደሚሉት ማህበሩ በተለይ ከ16ቱ ፀረ ጾታዊ ጥቃት ቀን ጀምሮ በማህበረሰቡ ዘንድ በዚህ መልኩ ግንዛቤ በመፍጠር የአመለካከት ለውጥ ለማምጣት እየሠራ ይገኛል:: እንደ ግጥም፤ ድራማ፤ መነባነብ፤ ጭውውት ያሉ ኪነ ጥበባዊ መንገዶችን በመጠቀምም ጥቃቱን ለማስቆም በሚያስችል ሂደት የበኩሉን ኃላፊነት እየተወጣ ይገኛል::

በሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የጽሕፈት ቤት ኃላፊዋ ወይዘሮ እታገኝ አሰፋ እንደሚናገሩት እንደ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤታቸው ዘላቂነት ባለው በዚህ መልኩ በቅንጅት መሥራት ጥቃቱን ይቀንስና ያስቆማል የሚል ዕምነት አለ:: በተለይ የሃይማኖት አባቶች በማህበረሰቡ ዘንድ ተሰሚነት ስላላቸው ትርጉም ያለው ውጤት ያመጣሉ ተብሎ ይጠበቃል:: በኪነ ጥበቡ መንገድም እንዲሁ ማህበረሰቡ እየተዝናና ጭምር ግንዛቤ ይጨብጣል የሚል እምነት አለ::

እንዲህ ዓይነቱን በሃይማኖት አባቶች፤ በኪነ ጥበቡ መስክ፤ እንደ ሴቶች ይችላሉ ባሉ ማህበራትና በተለያዩ አደረጃጀቶች በግልም ጭምር የሚደረግ ተግባሩን የማስቆም ዘላቂነት ያለው ጥረት በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ይበረታታል:: ከዚህ ባሻገር ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ጥቃቱን ለማስቆም ለየት ባለ ሁኔታ እየሠራ ነው:: በተለይ ሕጉ ጠበቅ እንዲል ትኩረት አድርጓል::

የሴቶችና የሕፃናት ጥቃት ከእለት ተእለት እየጨመረ ከመምጣቱ ጋር ተያይዞ ቀደም ሲል የነበረውን ሕግ በመፈተሽ ችግሩን ውጤታማ በሆነ መንገድ መከላከል የሚያስችል ተጨማሪና አስተማሪ ሕግ እየተረቀቀ ይገኛል:: ከዚህ ጎን ለጎንም ጥቃት አድራሾችን መመዝገብ የሚያስችል ዲጂታል የመረጃ ሥርዓት ከድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ ጋር በመሆን የማጎልበት ሥራ እየተሠራ ነው::


ወጣት ስንታየሁ ቤተማርያም፤


ወይዘሮ እታገኝ አሰፋ


ወይዘሮ እምወድሽ በቀለ

# ማረፊያ

## አዲስ ዘመን ድሮ

**ሙሉጌታ ብርሃኑ**

አዲስ ዘመን ድሮ፤ ካለፉ ትናንትናዎች ሰንቆ ለዛሬ ትውስታ ይሆኑን ዘንድ ሁሉንም ከዚህም ከዚያም እያለ ያስቃኘናል:: ሰሞነኛው በዓለ ጥምቀት እንደመሆኑ፣ ጥምቀትን በተመለከተ ከወጡ ዘገባዎች አንዱን አካተናል:: በመሐል አዲስ አበባ ጸብና ትንኮሳ የተያዘው “ዓመጸኛው ዝንጀሮ ተገደለ” ይለናል:: “22 ጠንቋዮች ራሳቸውን አጋለጡ” እንደምን ብለው ይሆን...ቦንቡን እብድ እንዳይተኩሰው ስጋት ገብቷል:: ሌላኛው በልቶ ጠፊ በሠፈሬ ካልተዳኘሁ ይላል:: ከተለመዱት የጳውሎስ ኞኞ “አንድ ጥያቄ አለኝ” ጥያቄና ምላሾች ጋር ለዛሬው መቆያ እንዲሆኑን ብለናል::

**በከፋ የጥምቀት በዓል በድምቀት ካልተከበረ ድኅነት ይወረሳል የሚለው ጎጂ ልማድ እየቀነሰ ነው ተባለ**

በደቡብ ክልል በከፋ ዞን “የጥምቀት በዓል በደማቅ ሁኔታ ካልተከበረ ድህነት ይወረሳል” በሚል አጉል ልማድ በዓሉን ለማክበር ሲባል ለልብስና ለተለያዩ ጌጣጌጥ መግዣ የሚወጡ ወጪዎችን ለመቀነስ የተካሄደው እንቅስቃሴ ውጤታማ መሆኑን የዞኑ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች አስወጋጅ ኮሚቴ አስታወቀ::

....

እያንዳንዱ አርሶ አደር ገንዘብ ባይኖረው ለበዓሉ በሬውን እስከ መሸጥ ይደርሳል ያሉት ምክትል ሰብሳቢው፤ በአቅም ማነስ ይህን መፈጸም ያልቻሉ አባወራዎች ትዳራቸውን እስከ ማፍረስ የሚገደዱበት አጋጣሚ መኖሩን ጠቁመዋል::

**(አዲስ ዘመን ጥር 12 ቀን 1994ዓ.ም)**

**ዓመጸኛው ዝንጀሮ ተገደለ**

ሁለት ቀን ሙሉ በመንደር ውስጥ እየተዘዋወረ በሰላማዊ ሰዎች ላይ ጉዳት ያደረሰው ዝንጀሮ ተገደለ::

በልደታ ወረዳ መካኒሳ ቀበሌ የመጣበት ያልታወቀ አንድ ገመሬ ዝንጀሮ መጋቢት 18 ቀንና መጋቢት 19 ቀን 7 ሰዎችን ነክሶ ከማቁሰሉም በላይ፤ በመንደሩ የሚገኙትን ውሾች በሙሉ እንዲባረሩ አድርጓል::

በዚሁ ዝንጀሮ ከተነከሱት 7 ሰዎች መካከል 4ቱ በብርቱ ስለቆሰሉ ለሕክምና ወደ ሆስፒታል መወሰዳቸውን ከአሜሪካ ሉተራን ሚሲዮን ቄስ ዓለም ታደሰ በላይ ገልጸዋል::.

ራሳቸውን ለመከላከል ከሞከሩት መካከል የስካንስካ ጋራዥ ሠራተኞች ትናንት በ11 ሰዓት ገደማ ላይ በሦስት ጥይት ከመቱት በኋላ ዝንጀሮው የሞተ መሆኑን ከሠፈርተኛው ለመረዳት ተችሏል::

በሠፈርተኛው ላይ ጉዳት ያደረሰው ዝንጀሮ እሬሳ አሁንም ከመካኒሳ በታች ከሚገኘው ወንዝ ዳር ተጥሎ ይገኛል::

**( አዲስ ዘመን ጥቅምት 15 ቀን 1976ዓ.ም)**

**22 ጠንቋዮች ራሳቸውን አጋለጡ**

ደሴ (ኢ.ዜ.አ) ወሎ ውስጥ በደላንታ ወረዳ የኢላና ትምህርት ቤት መምህራን ከጣርዳት፣ ከደህናንና ከዝባን የገበሬ ማኅበራት ጋር በመተባበር በመካከላቸው የተሰገሰጉትን 22 አባይ ጠንቋዮች ራሳቸውን አጋልጠው ክቡር ወደሆነው የሥራ መስክ እንዲሠማሩ አደረጉ።

እነዚሁ 22 አባይ ጠንቋዮች በተሰጣቸው ትምህርት አምነው ድቤዎችን(ከበሮዎችን)፣ እንዲሁም በእጃቸው ይገኙ የነበሩትን ልዩ ልዩ የጥንቆላ ዕቃዎችንና መጻሕፍት ለገበሬ ማኅበራቱ በራሳቸው ፈቃድ አስረክበዋል። አባይ ጠንቋዮቹ ካስረከቧቸው ዕቃዎች ውስጥ በተለይ ከበሮዎቹ በአካባቢው ለሚቋቋመው የኪነት ቡድን መገልገያ እንዲሆን መሰጠቱ ተገልጿል።

**( አዲስ ዘመን መጋቢት 23 ቀን 1971 ዓ.ም)**

**ቦንቡን ዕብድ እንዳይተኩሰው ጥንቃቄ ተደርጓል**

ቢትል፤ አንድ አዕምሮው ትክክል ያልሆነ ሰው በድንገት ተነስቶ የኒውክሌር ጦር መሣሪያዎችን ቃታ በመሳብ ዓለምን ከአደገኛ ሁኔታ ላይ እንዳይጥል አሜሪካ ጥብቅ ቁጥጥር ታደርጋለች ሲሉ፤ የአሜሪካ ፕሬዚዳንት በአንድ የእራት ግብዣ ላይ ተናግረዋል::

...

የኒውክሌር ጦር መሣሪያዎች እንዲተኮሱ የሚያዘው ፕሬዚዳንቱ ብቻ ነው:: ከእርሱም ጋር ሁለት ወይም ሦስት ሰዎች ይመካከራሉ::

...

መሣሪያዎቹም የኤሌክትሮኒክስ ቁልፎች ይገኙባቸዋል፤ እነዚህንም ቁልፎች ለመፍታት የሚቻለው በምስጢራዊ ዘዴ ነው:: ይህንንም አያያዛችንን በጥብቅ እንከታተላለን ሲሉ መናገራቸውን ሮይተር ገልጿል::

(አዲስ ዘመን የካቲት 13 ቀን 1957ዓ.ም)

**በሠፈሬ ልዳኝ**

ወንድማችን(የተፈጥሮ) ቤት ተከራይቶ በሚያዝያ 27 አደባባይ(አቅራቢያ) ይኖራል:: ራት ምሳውን የሚመገበው አዲስ ከተማ ካሉት ሆቴሎች ነው:: የልደታ ዕለት ሳይከፍል በመቅረቱ በአዲስ ከተማ ፍርድ ቤት ተከሰሰ:: መልስም እንዲሰጥ ጥያቄ ቢቀርብለት የምኖረው በሌላ ወረዳ ስለሆነ፤ በዚያው ልከሰስና መልስ እሰጣለሁ አለ:: ዳኛም “መብሉ ከኛ ሠፈር፣ ክሱ በሌላ መንደር፣ በል ውሰድና እሠር” ብለው ፈረዱ:: የቀረው ሐተታ ለአንባቢ::

ማሞ ውድነህ

**አንድ ጥያቄ አለኝ**

**-ይድረስ ለጳውሎስ ኞኞ**

*ከአምስቱ የፋንታ ቆርኪዎች አራቱን አግኝቼ ቲ ጎደለችኝ:: ይቺን ቆርኪ ከሌላ ወስጄ ወይም ገዝቼ ባቀርብ ራዲዮኑን ማግኘት አልችልም?

**ኃይሌ ፍታዊ(ከአሥመራ)**

-መቻል ትችላለህ:: ግን እስካሁን እሷን ያገኘ ሰው የለምና ከየት ታገኛለህ?

*ሀብታሞች የዕድር ገንዘብ ሳይከፍሉ ሲቀሩ የሚጠይቃቸው የለም:: እኔ ግን ደሀ በመሆኔ የእድር አልከፈልክም ብለው ከዕድር አስወጡኝ:: ለምን እንዲህ ያደርጋሉ?

**ኃይሉ ተፈራ(ከሂርና)**

- ተው ሌላ ጉዳይ ይኖር ይሆናል:: ከሌለ እናንተ የሂርና ሰዎች እባካችሁ እንዲህ አታድርጉ:: ባይሆን የዛሬውን ማሩትና ዳግመኛ አይለምደውም:: አንተም ዓመልህን አሳምረህ የእድርህን ገንዘብ እየከፈልክ ኑር::

*እነዚህ ወፍ ሳይንጫጫ እየመጡ የሚጮሁት ላሊበላ የሚባሉት ሌሊት እየተነሡ ካልጮሁ ይቆመጣሉ ይባላል:: ይህ ነገር እስከ ምን ድረስ እውነት እውነት ነው?

ሻለቃ አበራ ታቦር

-እስከ መጨረሻው ድረስ ውሸት ነው::

**( አዲስ ዘመን ጥቅምት 4 1961ዓ.ም)**

*ስለ ፍቅር ይጠይቁሃል:: የእውነትም የፍቅር ምርኮኞች ከሆኑ ይኸ ሁሉ የወንድና የሴት ጋለሞታ ለምን በዛ?

**ስንታየሁ መሰንበት(ከማዘጋጃ ቤት)**

- መቼም የፍቅር ዓይነቱ ብዙ ስለሆነ የኔዎቹ ጠያቂዎች የሚይዛቸው እያስወደደ የሚያለያየው ነው:: በዚሁ ላይ እባካችሁ ሰዎች የተዋደድነው ተጠፋፋን የሚለውን ጥያቄያችሁን ተውኝ:: እናንተ የምትተዋወቁት ያልተገናኛችሁ እኔ የት ብዬ እንዳገኝላችሁ ነው?

**( አዲስ ዘመን የካቲት 4 ቀን 1962ዓ.ም)**

# ዓለም አቀፍ

## የትራምፕ የመጀመሪያዎቹ ትዕዛዞች

ትራምፕ በመጀመሪያው የሥልጣን ቀናቸው በርካታ ትዕዛዞችን ለማስተላለፍ ቃል ገብተዋል። ለደጋፊዎች ንግግር ያደረጉት ትራምፕ ቃለ መሐላ በፈፀሙ በጥቂት ሰዓታት ውስጥ “በታሪካዊ ፍጥነት እና ጥንካሬ” እንደሚንቀሳቀሱ ተናግረዋል።

በዋሺንግተን ዲሲ በሺዎች ለሚቆጠሩ ደጋፊዎች ንግግር ያደረጉት ተመራጩ ፕሬዚዳንት በሚቀጥሉት አራት ዓመታት ሊሠሯቸው ያሰቧቸውን ተግባራት ዘርዝረው ካበቁ በኋላ ባለፈው ኅዳር ዲሞክራቶችን በምርጫ በመርታታቸው ደስታቸውን ሲገልፁ ተስተውለዋል።

ሪፐብሊካኑ ፖለቲከኛ ያላቸውን ፕሬዚዳንታዊ ኃይል ተጠቅመው ስደተኞችን በገፍ ለማባረር፣ የተፈጥሮ ጥበቃ ላይ የሚያተኩሩ መመሪያዎችን ለመቀነስ እና የስብጥር (ዳይቨርሲቲ) ፕሮግራሞችን ለማስቆም ቃል ገብተዋል።

ትራምፕ ከበዓለ ሲመታቸው በኋላ 200 ገደማ ትዕዛዞች ላይ ፊርማቸውን እንደሚያሰፍሩ ይጠበቃል። አንዳንዶቹ ትዕዛዞች እንደ ሕግ የሚቆጠሩ ሲሆን ሌሎች ደግሞ ፕሬዚዳንታዊ መመሪያዎች ናቸው።

“የባይደን አስተዳደር ያስተላለፋቸው ትዕዛዞች ይሰረዛሉ” ብለዋል ትራምፕ። የሰው ሠራሽ ክህሎትን ዕድገት የሚያፋጥን እንዲሁም ኢላን መስክ የሚመራው ዶጅ የተባለው መሥሪያ ቤት እንዲቋቋም የሚወጣ ትዕዛዝ እንደሚፈርሙ አሳውቀዋል።

በአውሮፓውያኑ 1963 ስለተገደሉት ጆን ኤፍ ኬኔዲ መረጃዎችን እንደሚለቁ፤ ወታደራዊ ኃይሉን ‘አይረን ዶም’ እንዲሠራ እንደሚያዙ እንዲሁም ብዝኃነት፣ እኩልነት እና አካታችነት የሚባሉ ፖሊሲዎችን ከጦር ሠራዊቱ እንደሚያስወግዱ ቃል ገብተዋል።

ለደጋፊዎቻቸው ባደረጉት ንግግር ፆታ የቀየሩ (ትራንስጀንደር) ሰዎች በሴቶች ስፖርት እንዳይሳተፉ እንደሚያደርጉ እና የትምህርትን ሥልጣን ለአሜሪካ ግዛቶች አሳልፈው እንደሚሰጡ ተናግረዋል። “እናንተን በጣም ደስተኛ የሚያደርጉ ብዙ ትዕዛዞች ማየታችሁ አይቀርም” ብለዋል።

የአሜሪካ ፕሬዚዳንቶች ሥልጣን ሲጨብጡ በመጀመሪያ ቀናቸው ትዕዛዝ ማስተላለፋቸው የተለመደ ቢሆንም ትራምፕ በቁጥር በርካታ ትዕዛዞችን ለማስተላለፍ ቃል ገብተዋል። አብዛኛዎቹም በፍርድ ቤት ሙግት እንደሚቀርብባቸው እንደሚጠበቅ ተገልጿል።



ትራምፕ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሕጋዊ ወረቀት የሌላቸውን ስደተኞች ከአሜሪካ እንደሚያባርሩ ቃል ገብተዋል። ነገር ግን የስደት ተንታኞች የትራምፕ ዕቅድ ብዙ ሕጋዊ፣ የሎጂስቲክ፣ የገንዘብ እንዲሁም የፖለቲካ እንድምታ አለው ሲል ቢቢሲ ዘግቧል።

## የብሪታንያ ሚሊየነሮች እየተሰደዱ እንደሆነ ተገለጸ

ከ10 ሺህ በላይ የብሪታንያ ሚሊየነሮች መሰደዳቸው ተገለጸ። ከዚህ በፊት አፍሪካን ጨምሮ በመላው ዓለም የሚገኙ ባለፀጋዎች ዋነኛ መዳረሻ የነበረችው ብሪታንያ አሁን ደግሞ እየተሰደዱባት ነው ተብሏል። በብሪታንያ ሥልጣን ላይ ያለው ሊበራል ፓርቲ እኤአ ከ2026 ጀምሮ የሚተገበር አዲስ የግብር ሕግ አስተዋውቋል። ባለፀጋዎች ካላቸው ሀብት ላይ የ20 በመቶ ግብር እንዲጣል የሚጠይቀው ይህ ሕግ በለንደን እና በሌሎች የሀገሪቱ ከተሞች ያሉ ባለፀጋዎች እንዲሰደዱ ምክንያት መሆኑን ዘ ታይምስ ዘግቧል።

በጠቅላይ ሚኒስትር ኬር ስታርመር የሚመራው መንግሥት የሀብት መጠናቸው አንድ ሚሊዮን ፓውንድ እና ከዛ በላይ ሀብት ባላቸው ሰዎች እና ኩባንያዎች ላይ የ20 በመቶ ግብር እንዲከፍሉ ይጠይቃል። ይህን ተከትሎም በተለይም ለብዙ ዓመታት ከትውልድ ትውልድ ሲተላለፉ የመጡ ኩባንያዎች በአዲሱ ሕግ ደስተኞች እንዳልሆኑም ተጠቅሷል።

እንደ ዘገባው ከሆነ በተጠናቀቀው የፈረንጆቹ 2024 ዓመት ውስጥ ብቻ 10 ሺህ 800 ሚሊየነሮች ብሪታንያን ለቀዋል። የተሰደዱት ባለፀጋዎች ብዛት በ2023 ዓመት ከነበረው ጋር ሲነጻጸርም በ157 በመቶ ጭማሪ አሳይቷል። ባለፀጋዎቹ ከብሪታንያ ወደ ጣሊያን፣ ስዊዘርላንድ እና የተባበሩት ዓረብ ኢምሬት እንደተሰደዱም ተገልጿል።

የባለፀጋዎቹ መሰደድ የብሪታንያን ኢኮኖሚ ይጎዳል የተባለ ሲሆን በተለይም መንግሥት ከግብር የሚሰበስበውን ገቢ ከመቀነሱ ባለፈ የሥራ ቅጥር እና ተያያዥ ችግሮችን ሊያባብስ እንደሚችልም ተገልጿል፡፡ ከብሪታንያ በመቀጠልም በቻይናም በርካታ ባለፀጋዎቿ ወደ ሌሎች ሀገራት ተሰደዋል መባሉን የዘገበው አል ዐይን ነው።

# ስፖርት





# ኢትዮጵያውያን አትሌቶች በሂውስተን ጎዳናዎች ድል ቀንቷቸዋል

**ብርሃን ፈይሳ**

በአሜሪካ ከሚደረጉ የጎዳና ላይ ዓመታዊ የሩጫ ውድድሮች መካከል አንዱ የሂውስተን ማራቶን፣ ግማሽ ማራቶን እና የ5 ኪሎ ሜትር ፉክክር ነው። በሺዎች የሚቆጠሩ ሯጮች በነዚህ የተለያዩ ርቀቶች የሚፎካከሩበት ውድድር ከትናንት በስቲያ በቴክሳስ ግዛት በምትገኘው ሂውስተን ተካሂዷል።

በተለያዩ ርቀቶች የሚደረገው የአንድ ቀን ውድድር በከተማዋ በነበረው ቀዝቃዛ እና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ ምክንያት ፉክክሩን ፈታኝ ያደርገዋል የሚል ስጋት የነበረ ቢሆንም አትሌቶች ሳይበገሩ ከፍተኛ ፉክክር አሳይተዋል። ኢትዮጵያውያን አትሌቶች ከፍተኛ የአሸናፊነት ግምት በተሰጣቸው የሂውስተን ግማሽ ማራቶን ውጤታማ ለመሆን ችለዋል። በዓለም አትሌቲክስ የወርቅ ደረጃ የተሰጠው ይህ ውድድር ባለፉት ዓመታት የኢትዮጵያውያን አትሌቶች የበላይነት ታይቶበታል። ዘንድሮም የኢትዮጵያውያን አትሌቶች አሸናፊነት ቀጥሏል። በሴቶች መካከል በተደረገው ፉክክር ለሦስተኛ ጊዜ በተከታታይ አሸናፊ በመሆንም የበላይነታቸውን አጠናክረዋል።

ድንቅ ፉክክር በተደረገበት ውድድር አትሌቶች ከአንድ እስከ ሦስት ባለው ደረጃ ተከታትለው የገቡበት ሁኔታ እጅግ የተቀራረበ በመሆኑ አሸናፊው የተለየው በሰከንዶች ልዩነት ነበር። አትሌት ሠናይት ጌታቸው የውድድሩ አሸናፊ ስትሆን ያስመዘገበችው ሰዓትም 1፡06፡05 ሆኗል። በፖርቶ፣ ሊዝበን እና ቦስተን ማራቶኖች ባለፉት ዓመታት የተሳተፈችው አትሌት ሠናይት አዲሱን የውድድር ዓመት በአሸናፊነት ጀምራለች። አሜሪካዊቷ ዌኒ ከላቲ ደግሞ 1፡06፡09 በሆነ ሰዓት ሁለተኛ ደረጃን የያዘች አትሌት ሆናለች። ሌላኛዋ ለአሸናፊነት ስትጠበቅ የነበረችው ኢትዮጵያዊት አትሌት ቡዜ ድሪባ ደግሞ 1፡06፡48 በሆነ ሰዓት ገብታለች። አትሌቷ በዚህ ውድድር ስትሳተፍ ይህ የመጀመሪያዋ አይደለም። እአአ በ2018 በግማሽ ማራቶን እንዲሁም በ2019 ማራቶን ተካፍላ አራተኛ ደረጃን በመያዝ ነበር ያጠቃለለችው። የአምናዋ አሸናፊ ሱቱሜ ከበደ 1ሰዓት ከ04 ደቂቃ ከ37 ሰከንድ በመግባት የውድድሩ ክብረወሰን ባለቤት መሆኗ ይታወሳል።



**አትሌት አዲሱ ጎበና አስደናቂ ፉክክር በታየበት የሂውስተን ግማሽ ማራቶን አሸንፏል፣**

በተመሳሳይ በግማሽ ማራቶን በወንዶች መካከል የተካሄደው ፉክክር በኢትዮጵያዊ አትሌት አሸናፊነት ተጠናቋል። የአምናው የዱባይ ማራቶን አሸናፊ አትሌት አዲሱ ጎበና በቀዳሚነት ሲያጠናቅቅ ፉክክሩ እንደ ሴቶቹ ሁሉ ከፍተኛ የአሸናፊነት ትንቅንቅ የተደረገበት ነበር። ከአንድ እስከ አራት ያለውን ደረጃ ይዞ ለማጠናቀቅ በነበረው ትንቅንቅ አትሌቶች በሰከንዶች ብቻ ነበር የተለያዩት። አሸናፊው አትሌት በ59 ደቂቃ ከ17 ሰከንድ ርቀቱን ሲያጠናቅቅ፣ አሜሪካዊው ተፎካካሪውም በተመሳሳይ ሰዓት ነበር ሩጫውን ያጠናቀቀው። ሁለቱ አትሌቶች በማይክሮ ሰከንዶች በመለያየታቸው ያልተጠበቀው ኮነር ማትዝ ሁለተኛ ደረጃን መያዙ ተረጋግጧል። ታንዛኒያዊው ጋብሬል ጋይ ሦስተኛ እንዲሁም እአአ በ2020 የሂውስተን ማራቶን አሸናፊ የነበረውና ከዘንድሮ ተሳታፊዎች ቀዳሚው ፈጣን ሰዓት የነበረው ኢትዮጵያዊው አትሌት ጀማል ይመር ከፍተኛ የአሸናፊነት ፉክክር ቢያደርግም አራተኛ ደረጃን ይዞ ፈፅሟል።

በዚህ የግማሽ ማራቶን ውድድር ኢትዮጵያውያን አትሌቶች በተከታታይ አሸናፊ ሲሆኑም ይህ ለስድስተኛ ጊዜ ነው። በርካታ ታዋቂና ሀገራቸውንም በማራቶን ጭምር በስኬታማነት ማስጠራት የቻሉ አትሌቶችም በሂውስተን ግማሽ ማራቶን ተካፍለው እንደነበር ይታወቃል።

ኢትዮጵያውያን አትሌቶች በሂውስተን በማራቶን ላቅ ያለ ተሳትፎ ይኑራቸው እንጂ በተለይም በወንዶች ያለፉት ዓመታት የነበራቸው ተፎካካሪነት እየቀነሰ መጥቷል። በአንጻሩ በሴቶች በኩል አስደናቂ በሆነ መልኩ እአአ ከ2007 አንስቶ እስከ 2020 ድረስ አሸናፊዎቹ ኢትዮጵያውያን አትሌቶች ነበሩ። ባለፈው ዓመትም አትሌት ራህማ ቱሳ በቀዳሚነት ውድድሩን ልትፈጽም ችላለች።

ከትላንት በስቲያ በነበረው የሂውስተን ማራቶንም ኩመሺ ሲጫላ የኢትዮጵያውያኑን አትሌቶች አሸናፊነት ልታስቀጥል ችላለች። አትሌቷ ተፎካካሪዎቿን ከሁለት ደቂቃ በላይ ቀድማ 2 ሰዓት ከ20 ደቂቃ ከ42 ሰከንድ በሆነ ሰዓት አሸናፊ ሆናለች። የሀገሯ ልጆች ጽጌ ኃይለሥላሴ እና አና ዲባባ ደግሞ ሦስተኛ እና አራተኛ ደረጃን ይዘዋል።


ሕብረት ባንክ Hibret Bank

**Invitation to Bid**

**Bid No. HB/021/2025**

Hibret Bank would like to invite interested & eligible venders to bid for the supply of the following COMPUTER & Related Items.

| S/N | Description | Unit | Qty |
|---|---|---|---|
| 1 | CISCO Access Switch 24 TC-L | Pcs | 15 |
| 2 | Desktop Computer Type II | Pcs | 6 |
| 3 | Desktop Computer Type (21 inch) | Pcs | 4 |
| 4 | Laser Jet Printer (A3) | Pcs | 1 |
| 5 | Heavy Duty Photo/Document Scanner | Pcs | 1 |
| 6 | UPS 5KVA | Pcs | 12 |
| 7 | UPS 8KVA | Pcs | 12 |
| 8 | Multi-Function Printer & Copy Machine | Pcs | 1 |

Interested bidders shall submit their proposals as per the following conditions.

1. A Complete set of Bidding documents can be purchased by interested bidders upon payment (depositing) of non-refundable fee of Birr 200.00 (Two hundred) in Account Number IN0403007, in any branch of Hibret Bank; nearest and convenient to you after 2 (two) days of this bid announcement for the first time.
2. Bidders can obtain the bid document from Procurement Division which is located at Lideta sub city, Woreda 08, Ras Abebe Aregay Street, in front of Addis Abeba University School of Commerce, Hibir Tower, 19th floor.
3. Interested bidders are advised to review the bid document carefully before preparing & submitting their bids.
4. Bids must be submitted on February 5, 2025 until 2:00 PM at Hibret Bank Head Office, Procurement Division Hiber Tower 19th floor.
5. Each bid must be presented in a sealed envelope and strictly in accordance with the instruction to bidders indicated in the bid document.
6. The bid will be opened at Hibret Bank Head Office located at Lideta sub city, Woreda 08. Ras Abebe Aregay street, Hibir Tower, 4th floor at presence of bidders or their representative who choose to attend in the bid opening on February 5, 2025 at 2:45 P.M
7. Failure to observe the instructions & conditions provided in the bid document will constitute grounds for rejection of the bidder from competition
8. The Bank reserves the right to accept or reject the bid partly or totally
9. For additional information bidders can contact by the following address.

Tel 011 465 5222 ext. 212 and 211 or 011 470 6541

**Hibret Bank**

**የንግድ ምልክት እድሳት ማስታወቂያ**

1. የንግድ ምልክት ባለቤት፡ Arma Ltd

አድራሻ: Level 5, tower III, Nexteracom tower, Cybercity, Ebene, Mauritius

2. የማመልከቻ ቁጥር፡ FTM/8992
3. የጥበቃ ጊዜው፣ 5/10/2024 እስከ 5/10/2031
4. የንግድምልክት፡

5 ባለቤቱ የንግድ ምልክቱን የሚጠቀምበት በአዲስ ዘመን ጋዜጣ በ28/3/2010 Vol.LXXVI No.088 በወጣው ማስታወቂያ ላይ ለተዘረዘሩት ዕቃዎችና አገልግሎቶች ነው :

6.ይህ የንግድ ምልክት የታደሰ በመሆኑም ማንኛውም ሰው ካለባለቤቱ ፍቃድ ውጭ በዚህ የንግድ ምልክት ከተጠቀመ በኢትዮጵያ ህግ ይጠየቃል፡፡

**የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ባለስልጣን**

ADDIS ZEMEN VOI-LXXXIV-No.133-13/5/2017 (21/1/2025)

**የንግድ ምልክት እድሳት ማስታወቂያ**

1. የንግድ ምልክት ባለቤት፡ Arma Ltd

አድራሻ፡ Level 5, tower III, Nexteracom tower, Cybercity, Ebene, Mauritius

2. የማመልከቻ ቁጥር፡ FTM/8990
3. የጥበቃ ጊዜው፡ 5/10/2024 እስከ 5/10/2031
4. የንግድምልክት፡
5. ባለቤቱ የንግድ ምልክቱን የሚጠቀምበት በአዲስ ዘመን ጋዜጣ በቀን 28/3/2010 Vo. LXXVII No.088 በወጣው ማስታወቂያ ላይ ለተዘረዘሩት ዕቃዎችና አገልግሎቶች ነው።
6. ይህ የንግድ ምልክት የታደሰ በመሆኑም ማንኛውም ሰው ካለባለቤቱ ፍቃድ ውጭ በዚህ የንግድ ምልክት ከተጠቀመ በኢትዮጵያ ህግ ይጠየቃል፡፡

**የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ባለስልጣን**

ADDIS ZEMEN VOI-LXXXIV-No.133-13/5/2017 (21/1/2025)

**አዲስ አበባ አስተዳደር**

አመልካች፡- ወ/ሮ መዲና ኢሳ ኩማንዴ ተጠሪ ፡- አቶ ኢብራሂም ዳኜ አህመድ መካከል ስላለው የባልና ሚስት የፍች ውጤት ጉዳይ ተጠሪ በ19/5/2017 ዓ.ም ለሆነው ቀጠሮ ፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍ/ቤት 2ኛ ችሎት ፍትሐብሔር ችሎት ከጠዋቱ በ3፡00 ሰዓት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**ፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍ/ቤት**

**አማራ ክልል**

በከሳሽ ዘመናይ ዘለቀ በተከሳሽ አቶ ባየች እንቢአለ መካከል ባለው የባልና ሚስት ክስ ጉዳይ ተከሳሽ ለጥር 26 ቀን 2017 ዓ.ም ከጠዋቱ 3፡30 ሰዓት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍ/ቤት**

**የባሕር ዳር ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት**